1. A certified copy of the Bank's Memorandum of Association and Articles of Association.

እናት ባንክ አክሲዮን ማኅበር

መመሥረቻ ጽሑፍ

እኛ ስማችን፣ ዜግነታችን፣ አድራሻችንና የአክሲዮን ይዞታችን ብዛት ከዚህ ሰነድ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ላይ የተገለፀው የእናት ባንክ አክሲዮን ማኅበር መሥራቾች በ1952 ዓ/ም በወጣው የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ፣ በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000፣ በመመሥረቻ ጽሑፉና በመተዳደሪያ ደንቡ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣቸውና ወደፊትም በሚያወጣቸው ደንቦችና መመሪያዎች ለመገዛትና ለመተዳደር ወስነን የባንኩን ካፒታል ለማዋጣትና በየስማችን አቅጣጫ የተመለከተውን የአክሲዮን ብዛት ለመግዛት ወደንና ፈቅደን መፈረማችንና ግዴታ መግባታችንን እናረጋግጣለን።

የስምሪት ሪፒፖርቲንግ መረጃ ዴስክ ዋና መ/ቤት
የተመራበት ክፍል 311ርርሮ
የተመራበት ቀን 23/04/04
ስምና ፊርማ

አንቀጽ 1. የባንኩ ስም

ባንኩ "እናት ባንክ አክሲዮን ማኅበር" እየተባለ ይጠራል።

አንቀጽ 2. ዋና መሥሪያ ቤት

(1) የባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ቦሌ ክ/ከተማ፣ ቀበሌ 03/05 የቤት ቁጥር 074 ሲሆን፣ አድራሻው እንደ አስፈላጊነቱ ሊለወጥ ይችላል።

(2) ባንኩ እንደ አስፈላጊነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ለባንክ ሥራ ተስማሚ በሆኑ ቦታዎች ቅርንጫፎች ሊከፍት ይችላል።

(3) እንዲሁም፣ የድሬክተሮች ቦርድ ሲወስንና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሲፈቅድ ባንኩ በውጭ አገር ቅርንጫፍ ሊከፍት ይችላል።

አንቀጽ 3. የባንኩ ዓላማዎች

ባንኩ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

(1) በተጠየቀ ጊዜ የሚከፈል፣ የቁጠባና በጊዜ ገደብ የሚቀመጥ ገንዘብ መቀበልና የተለያዩ ብድሮች፣ ተቀዳሚ ክፍያዎችና ኦቨርድራፍት አገልግሎት መስጠት፤

(2) የውጭ ምንዛሪ መግዛትና መሸጥ፤

(3) ባገር ውስጥና በውጭ አገር ላሉ ሰዎች በባንኩ እና በደንበኞቹ ስም ገንዘብ ማስተላለፍ፤

(4) የሌሎች ባንኮችና ኢንቬስተሮች ወኪል ወይም ባለአደራ ሆኖ መሥራት፤

(5) ንብረት በባለቤትነት፣ በኪራይ ወይም በማናቸውም ሕጋዊ መንገድ መያዝ፤

(6) ለንግድ ዓላማው ገንዘብ መበደር፣ ውል መዋዋልና ሌሎች ሕጋዊ ተግባሮችን ሁሉ ማከናወን፤

(7) ሴቶች የተሟላ የባንክ አገልግሎት እንዲያገኙ ቅድሚያ ማድረግ፤ እንዲሁም፤ ሴቶች

The FDRE Ministry of Justice Documents Authentication and Registration Office

የልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑና በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ የሚከናወኑ የልማትና የማኅበራዊ እንቅስቃሴዎችን ማገዝ፡፡

አንቀጽ 4. የአክሲዮን ካፒታል

(1) የባንኩ የተፈረመ የአክሲዮን ካፒታል ብር 249,979,000.00 (ሁለት መቶ አርባ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺህ) ሲሆን፣ የእያንዳንዱ አክሲዮን ዋጋ (par value) ብር 1,000 (አንድ ሺህ) በሆነ 249,979 (ሁለት መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ዘጠኝ) ተራ አክሲዮኖች (ordinary shares) የተከፋፈለ ነው፡፡

(2) ከባንኩ የተፈረመ የአክሲዮን ካፒታል ውስጥ ብር 109,532,665.00 (አንድ መቶ ዘጠኝ ሚሊዮን አምስት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ አምስት) በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል፡፡

(3) ከተፈረመው የአክሲዮን ካፒታል ውስጥ ያልተከፈለው ቀሪ ገንዘብ የባንኩ መቋቋም ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በሦስት ዓመት ውስጥ የቀሪውን ገንዘብ ቢያንስ ሃያ አምስት በመቶ (25%) በየዓመቱ በመክፈል ይጠናቀቃል፡፡

አንቀጽ 5. የአክሲዮን ይዞታ

(1) የባንኩ አክሲዮኖች በባለአክሲዮኑ ስም የተመዘገቡ፣ እኩል ዋጋ ያላቸውና ተራ አክሲዮኖች ይሆናሉ፡፡

(2) ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች አክሲዮን በጋራ ለመግዛት ይችላሉ፡፡ እንደዚህ በሚሆንበት ጊዜ፣ በባንኩ ጠቅላላ ጉባዔዎች የሚሳተፈው ከመካከላቸው አንድ ሰው ብቻ ይሆናል፡፡

(3) የባንኩ ባለአክሲዮን መሆን የሚችሉት ኢትዮጵያውያን እና አክሲዮናቸው ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ባለቤትነት የተያዙ ድርጅቶች ብቻ ናቸው፡፡

(4) ማንኛውም ባለአክሲዮን ብቻውን ወይም ከባለቤቱ (spouse) ወይም አንደኛ ደረጃ የሥጋ ዝምድና ካላቸው ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ ዘመዶቹ ጋር በመሆን ከባንኩ ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል ከአምስት በመቶ (5%) በላይ ለመያዝ አይችልም፡፡

(5) በሌላ ባንክ ውስጥ ከተፈረመው ካፒታል ሁለት በመቶ (2%) ወይም በላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ አክሲዮን የያዘ ሰው በባንኩ አክሲዮን ለመያዝ አይችልም፡፡

(6) አክሲዮን ለሌላ የሚተላለፈው በባንኩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 5 መሠረት ይሆናል፡፡

The FDRE Ministry of Justice Documents Authentication and Registration Office-A

<u>አንቀጽ 6. የአክሲዮኖች መዝገብ</u>

(1) ባንኩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሠረት የባለአክሲዮኖችን ስም ዝርዝር እና ድምፅ የመስጠት መብታቸውን የሚያሳይ የአክሲዮን መዝገብ ይይዛል፡፡

(2) መዝገቡ የባለአክሲዮችን ስም፣ አድራሻ፣ የገዙትን የአክሲዮን ብዛትና መለያ ቁጥር፣ የከፈሉትን የገንዘብ መጠንና የተመዘገቡበትን ቀን መያዝ አለበት፡፡

(3) መዝገቡ ማናቸውም ሰው ያለክፍያ ሊመለከተው እንዲችል በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት በመደበኛ የሥራ ሰዓት ክፍት መሆን አለበት፡፡

<u>አንቀጽ 7. የአክሲዮን ሰርተፍኬት</u>

(1) የባንኩን አክሲዮን ለመግዛት የፈረመ ሰው የአክሲዮኑን ሙሉ ዋጋ ከፍሎ ሲጨርስ በንግድ ሕግ ቁጥር 330 መሠረት የተዘጋጀና የታተመ የአክሲዮን ሰርተፍኬት ይሰጠዋል፡፡

(2) እያንዳንዱ ሰርተፍኬት በድሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበርና በባንኩ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ተፈርሞ የባንኩ ማሕተም ይታተምበታል፡፡

(3) የአክሲዮን ሰርተፍኬቱ ቢበላሽ ወይም ቢጠፋ የድሬክተሮች ቦርድ የሚወስነውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ለባለአክሲዮኑ ሌላ የአክሲዮን ሰርተፍኬት ተዘጋጅቶ ይሰጠዋል፡፡

<u>አንቀጽ 8. የትርፍ ክፍፍል</u>

ለባለአክሲዮኖች ትርፍ የሚከፋፈለው በባንኩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 34 መሠረት ይሆናል፡፡

<u>አንቀጽ 9. መስራቾች</u>

በንግድ ህግ ቁጥር 307 መሠረት መሥራቾች የሚባሉት በንዑስ አንቀጽ 2፣3 እና 4 የተዘረዘሩት በሙሉ ናቸው፡፡

<u>አንቀጽ 10. የመሥራች ባለአክሲዮኖች ጥቅም</u>

የባንኩ መሥራቾች በባንኩ ምሥረታ ወቅት ላደረጉት አስተዋጽኦና ለወሰዱት ኃላፊነት ከባንኩ የተጣራ ትርፍ ላይ በየዓመቱ አምስት በመቶ (5%) የማግኘት መብት አላቸው፡፡ ይህም ክፍያ የሚፈፀመውም ባንኩ ትርፋማ ሆኖ ለባለአክሲዮኖቹ የትርፍ ድርሻ (Dividend) መክፈል ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ሦስት ትርፋማ ተከታታይ ዓመታት ይሆናል፡፡

አንቀጽ 11. የባንኩ አካላት

ባንኩ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፤

(1) የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ

(2) የዲሬክተሮች ቦርድ

(3) የባንኩ ፕሬዝዳንት

(4) የባንኩ የውጭ ኦዲተር

አንቀጽ 12. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ

(1) የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የባንኩ የበላይ አካል ሲሆን፣ በመተዳደሪያ ደንቡ፣ በንግድ ሕጉና አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተሰጡ ሥልጣኖች ይኖሩታል።

(2) የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ፣ በንግድ ሕግና በባንኩ መተዳደሪያ ደንብ ከአንቀጽ 6 እስከ 16 በተወሰነው መሠረት ይካሄዳል።

አንቀጽ 13. የዲሬክተሮች ቦርድ

(1) ባንኩ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በሚመረጡ አሥራ አንድ አባላት ባሉት የዲሬክተሮች ቦርድ ይመራል። የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 17 የተገለፀው እና በሕግ የተወሰነው ይሆናል።

(2) ሹመታቸውን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በጽሑፍ የሚሰጠው ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከዚህ በታች ስማቸው የተጠቀሰው ባለአክሲዮኖች የመጀመሪያዎቹ የባንኩ የድሬክተሮች ቦርድ አባላት ሆነው ለሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት እንዲያገለግሉ ተመርጠዋል።

2.1 ወ/ሮ መዓዛ አሸናፊ መንግሥቱ
2.2 ወ/ሮ አስቴር ሰለሞን ንዋይ
2.3 ወ/ሮ ንግሥት ኃይሌ ጎሹ
2.4 ዶ/ር አሰፋ በቀለ ለሙ
2.5 አቶ ጫንያለው ይልማ አሻግሬ
2.6 አቶ ፀጋዬ ተጠምቀ ገ/እዝጊ
2.7 አቶ ንጋቱ ተስፋዬ ሀብተይመር
2.8 ወ/ሮ ነፃነት መንግሥቱ አልማው
2.9 ዶ/ር ካሣሁን እበሩ ወ/አማኑኤል
2.10 ወ/ሮ ቆንጂት ሰነጋዮርጊስ ወ/ማርያም
2.11 አቶ መክተ ሽፈራው ጎንጤ

The FDRE Ministry of Justice Documents Authentication and Registration Office

2.11 አቶ መከተ ሽፈራው ንጉሤ

አንቀጽ 14. የባንኩ ፕሬዝዳንት

የባንኩ ፕሬዝዳንት በባንኩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 23 እና በሌሎች ሕጎች የተመለከተው ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል። ቦርዱም እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው ሌሎች ሥልጣኖችንና ኃላፊነቶችን ሊሰጠው ይችላል።

አንቀጽ 15. የባንኩ የውጭ ኦዲተር

የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያለው የውጭ ኦዲተር ይመርጣል። የኦዲተሩ ተግባርና ኃላፊነት በንግድ ሕግ ድንጋጌዎች እና በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 24 የተመለከተው ይሆናል።

አንቀጽ 16. የዋስትና አክስዮኖች

ድሬክተሮች ኃላፊነታቸውንና ተግባራቸውን በትክክልና በሚገባ ለመወጣታቸው ዋስትና እንዲሆን እያንዳንዱ ድሬክተር አራት የተመዘገቡ አክሲዮኖችን በባንኩ ያስቀምጣል። ድሬክተሩ ከኃላፊነቱ ካልለቀቀና ባንኩ በኃላፊነት እንደማይጠይቀው ካልተረጋገጠ በስተቀር በባንኩ ዘንድ የተቀመጡት አክሲዮኖች ለድሬክተሩ አይመለሱም። ሆኖም፤ ድሬክተሩ አክሲዮኖቹ የሚያስገኙትን የትርፍ ድርሻ የማግኘት መብት አለው።

አንቀጽ 17. የሂሳብ አያያዝ

የባንኩ ሂሳብ አያያዝ በባንኩ መተዳደሪያ ደንብ ከአንቀጽ 25 እስከ 33 በተመለከተው መሠረት ይሆናል።

አንቀጽ 18. ምዝገባና ሪፖርቶችን ይፋ ስለማድረግ

(1) በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍና በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የሚደረግ ማናቸውም ማሻሻያ በባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ከጸደቀ በኋላ በንግድ ሕግ ቁጥር 222 እና 224 በተደነገገው መሠረት ይመዘገባል።

(2) የባንኩ ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 35 በተገለጸው መሠረት ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል።

አንቀጽ 19. የባንኩ መፍረስና ንብረት ማጣራት

ባንኩ የሚፈርሰውና ንብረቱ የሚጣራው ሕግ በሚደነግገውና በባንኩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 መሠረት ይሆናል።

አንቀጽ 20. ባንኩ የሚቆይበት ጊዜ

ባንኩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው።

አንቀጽ 21. የመመሥረቻ ጽሑፉን ስለማሻሻል

የባለአክስዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በባንኩ የመመሥረቻ ጽሁፍ ላይ የሚያደርገው ማሻሻያ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት።

አንቀጽ 22. መመሥረቻ ጽሑፉ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የመመሥረቻ ጽሑፍ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይሁንታ አግኝቶ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

በኢፌዴሪ የፍትህ ሚኒስቴር
የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት
አዲስ አበባ (ዋናው መሥሪያ ቤት)

ቁጥር ቀ/ጠ/2821/4ሀ/2005

በጽሕፈት ቤቱ ቀርበው ፈርመዋል።

አዲስ አበባ 02/02 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዶርጋ ታደሰ
የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ
ጽ/ቤት ሀላፊ

The F.D.R.E. Ministry of Justice Documents Authentication and Registration Office

[illegible] ሚኒስቴር
[illegible] ምዝገባ ጽ/ቤት
[illegible] ማረጋገጫ [illegible]
[illegible] 13258
[illegible] ተመዝግቦ ተለጥፏል።
[illegible] 3117891
9/2 ቀን 20 05 ዓ.ም.

የእናት ባንክ አክሲዮን ማኅበር

የተሻሻለ የመመስረቻ ጽሑፍ

ማውጫ

መግቢያ 1

ምዕራፍ አንድ፡ ጠቅላላ ድንጋጌዎች 1

አንቀጽ 1. የባንኩ ስም 1

አንቀጽ 2. ዋና መሥሪያ ቤት 1

አንቀጽ 3. የባንኩ የስራ መስክ እና ዓላማዎች 1

አንቀጽ 4. ገደቦች 1

ምዕራፍ ሁለት፡ ስለአክሲዮን፣ የባለአክሲዮኖች መብትና ግዴታ 4

አንቀጽ 5 የባንኩ ካፒታል 4

አንቀጽ 6. የአክሲዮን ይዞታ 4

አንቀጽ 7. የባለአክሲዮኖች መብትና ግዴታ 5

አንቀጽ 8. አክሲዮኖችን ለሌላ ስለማስተላለፍ 6

አንቀጽ 9. የአክሲዮኖች መዝገብ 6

አንቀጽ 10. የአክሲዮን ግዑዝ አልባ መሆን 7

ምዕራፍ ሦስት፡ የባንኩ አደረጃጀት 7

አንቀጽ 11. የባንኩ አካላት 7

አንቀጽ 12. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ 8

አንቀጽ 13. የዳይሬክተሮች ቦርድ 8

አንቀጽ 14. ዋና ሥራ አስፈጻሚ 8

አንቀጽ 15. የውጭ ኦዲተር 9

አንቀጽ 16. የማህበሩ ፀሐፊ 9

ምዕራፍ አራት፡ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ 9

አንቀጽ 17. ጠቅላላ ደንቦች 9

አንቀጽ 18. የጠቅላላ ጉባዔ 10

አንቀጽ 19. የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ማስታወቂያ 10

አንቀጽ 20. የውክልና ሰነዶች የሚቀርቡበት የጊዜ ገደብ 10

አንቀጽ 21. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ 10

አንቀጽ 22. የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ምልዐተ ጉባዔ (Quorum) እና የውሳኔ አሰጣጥ 11

አንቀጽ 23. አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ 11

አንቀጽ 24. የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ምልዐተ ጉባዔና የውሳኔ አሰጣጥ 12

አንቀጽ 25. የጉባዔው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ 13

አንቀጽ 26. የጥቅም ግጭት 13
አንቀጽ 27. ቃለጉባዔዎች 14
አንቀጽ 28. በጠቅላላ ጉባዔ በተሰጡ ውሣኔዎች ላይ መቃወሚያ ስለማቅረብ 14
ምዕራፍ አምስት፡ የዳይሬክተሮች ቦርድ 15
አንቀጽ 29. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባር 15
አንቀጽ 30. ለባንኩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች መዝገብ 18
አንቀጽ 31. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ 18
አንቀጽ 32. የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ 19
አንቀጽ 33. ዳይሬክተሮችን ስለመተካት 19
አንቀጽ 34. የዳይሬክተሮች ክፍያ 20
አንቀጽ 35. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ተጠያቂነት 20
አንቀጽ 36. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ስለመሻር 21
አንቀጽ 37. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን የሥራ ዘመን 21
ምዕራፍ ስድስት፡ ዋና ሥራ አስፈጻሚ 26
አንቀጽ 38. የዋና ሥራ አስፈጻሚ ሥልጣንና ተግባር 22
ምዕራፍ ሰባት፡ 29
አንቀጽ 39. የውጪ ኦዲተር 25
ምዕራፍ ስምንት፡ የማህበሩ ፀሐፊ 29
አንቀጽ 40. የማበሩ ፀሐፊ 25
ምዕራፍ ስጠኝ፡ የሂሣብ አያያዝና ተዛማጅ ተግባራት 26
አንቀጽ 41. ጠቅላላ መመሪያዎች 26
አንቀጽ 42. የፋይናንስ መዝገቦችና መረጃዎች 26
አንቀጽ 43 የሂሣብ ዓመትና ሪፖርት 26
አንቀጽ 44. የሂሣብ ሰነዶችና ሪፖርት ለኦዲተሮች ስለማቅረብ 26
አንቀጽ 45. የሂሣብ ሚዛንና የትርፍና ኪሳራ መግለጫ 26
አንቀጽ 46. የማይነካ ካፒታልና ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሣብ ስለመያዝ 27
አንቀጽ 47. በጥሬ ገንዘብ ስለሚያዙ ሂሣቦችና የመጠባበቂያ ገንዘብ ሚዛን 27
አንቀጽ 48. በቸልተኝነት ወይም እምነት በማጉደል ለሚከሰቱ ኪሣራዎች መጠባበቂያዎች 27
አንቀጽ 49. ሌሎች የመጠባበቂያ ሂሣቦች 28
አንቀጽ 50. የትርፍ ድርሻ አመዳደብና አከፋፈል 28
አንቀጽ 51. የሂሣብ ሚዛን ይፋ ስለማድረግ 28

ምዕራፍ አስር፡ የባንኩን ካፒታል ማሳደግ ወይም መቀነስ.......... 29
አንቀጽ 52. ካፒታል ስለ ማሳደግ.......... 29
አንቀጽ 53. የቅድሚያ መብት.......... 30
አንቀጽ 54. የአዲስ አክሲዮኖችን ሽያጭ የሚመለከት መረጃ ስለመያዝ.......... 30
አንቀጽ 55. የካፒታል መቀነስ.......... 30
ምዕራፍ አስራ አንድ፡ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች.......... 30
አንቀጽ 56. ባንኩ የሚቆይበት ጊዜ.......... 30
አንቀጽ 57. ከባንኩ የመውጣት መብት.......... 30
አንቀጽ 58. ባንኩን ለመፍረስ የሚያበቁ ምክንያቶች.......... 31
አንቀጽ 59. በመመስረቻ ጽሁፉ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች.......... 31
አንቀጽ 60. የመመስረቻ ጽሁፉን ስለማሻሻል.......... 31
አንቀጽ 61. የተሻሩ ድጋጌዎች.......... 32
አንቀፅ 62 መመስረቻ ፅሑፉ የሚፀናበት ጊዜ.......... 32
አንቀፅ 63 የባንኩ ባለአክሲዮኖች ስም ዝርዝር፣ አደራሻ፣ ዜግነትና የአክሲዮን መጠን.......... 32

መግቢያ

እናት ባንክ አክሲዮን ማኅበር (ከዚህ በኋላ "ባንኩ" ወይም "ማኅበሩ" እየተባለ የሚጠራው) በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ፣ የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 (በአዋጅ ቁጥር 1159/2011 እንደተሻሻለው) ፣በንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 እና አግባብነት ባላቸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መሰረት ተቋቁሞ የባንክ ንግድ ሥራ በማከናወን ላይ ይገኛል።

በቅርብ ዓመታት በሀገራችን የፋይናንስ ሴክተር ፈጣን የሆኑ የፖሊሲ እና የሕግ ማዕቀፍ ለውጦች እየተከናወኑ ይገኛሉ። በመሆኑም ባንኩ ከለውጦቹ ጋር ለመራመድና ራሱን በማሻሻል ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲቀጥል ለማስቻል እና ሕጋዊ ተገዢነቱን ለማረጋገጥ ያሉትን ነባራዊ ለውጦች መሠረት በማድረግ መመስረቻ ጽሁፉን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የባንኩ ባለአክሲዮኖች በ3ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ፣ ታህሳስ 11 ቀን 2018 ዓ.ም ይህንን የተሻሻለ የመመስረቻ ጽሑፍ አጽድቀናል።

ምዕራፍ አንድ፡ ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 1. የባንኩ ስም

ባንኩ "**እናት ባንክ አክሲዮን ማኅበር**" እየተባለ ይጠራል።

አንቀጽ 2. ዋና መሥሪያ ቤት

1. የባንኩ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 8 የቤት ቁጥር አዲስ ሲሆን፤ አድራሻው እንደ አስፈላጊነቱ ሊለውጥ ይችላል።
2. ባንኩ እንደ አስፈላጊነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ለባንክ ሥራ ተስማሚ በሆኑ ቦታዎች ቅርንጫፎችና ንዑስ ቅርንጫፎች ሊከፍት ይችላል።
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሲወስንና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሲፈቅድ ባንኩ በውጭ ሀገር ቅርንጫፍ ወይም ተቀጽላ ሊከፍት ይችላል።

አንቀጽ 3. የባንኩ ዓላማዎች እና የስራ መስክ

ባንኩ የሚከተሉት ዓላማዎች እና የስራ መስክ ይኖሩታል፤

1. በተጠየቀ ጊዜ የሚከፈል፣ የቁጠባና በጊዜ ገደብ የሚቀመጥ ገንዘብ መቀበልና የተለያዩ ብድሮች፣ ተቀዳሚ ክፍያዎችና ኦቨርድራፍት አገልግሎት መስጠት፤
2. በሀገር ውስጥና በውጭ አገር ላሉ ሰዎች በባንኩ እና በደንበኞቹ ስም ገንዘብ ማስተላለፍ፤

3. የሌሎች ባንኮችና ኢንቬስተሮች ወኪል ወይም ባለአደራ ሆኖ መስራት፤

4. ንብረት በባለቤትነት፣ በኪራይ ወይም በማናቸውም ሕጋዊ መንገድ መያዝ፤

5. ሥራውን ለማካሄድ የሚያስፈልገውን ገንዘብ የማህበሩን ንብረቶች በዋስትና በማስያዝ ወይም ያለዋስትና ይበደራል፤ ውል መዋዋልና ሌሎች ሕጋዊ ተግባሮችን ሁሉ ማከናወን፤

6. የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ አቅም በማጎልበት ላይ በማተኮር ጥራት ያለው እና ሁሉን አካታች የባንክ አገልግሎት መስጠት፤

7. የተለያዩ ብድሮችን፣ የተለያዩ የፋይናንስ ዋስትናዎችን (Guarantees) እና የክሬዲት ደብዳቤዎችን (Letters of Credit) መፍቀድ፤

8. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ እና በብሔራዊ ባንክ የዉጪ ምንዛሬ መመሪያ መሠረት የውጭ ሀገር ገንዘብ ይገዛል፤ ይሸጣል፤ ይይዛል፤ ከውጭ ምንዛሬ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ማናቸውንም ሥራዎች መስራት፤

9. የኢትዮጵያ መንግስት የሚያወጣቸውን የሚተላለፉ የንግድ ሰነዶች፣ የገንዘብ ዋስትና የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች፣ እንዲሁም ባንኩ ለሰጣቸው ብድሮችና ሰነዶች፣ቅድሚያ ክፍያዎች በዋስትና የተያዙ ሌሎች ንብረቶችን ሁሉ መያዝ፣መግዛት፣ መሸጥ፤

10. ሰነዶችን፣ ዕንቁዎችን፣ የከበሩ ድንጋዮችንና ዋጋ ያላቸውን ሌሎች ነገሮች የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ተቀብሎ በአስተማማኝ ካዝናዎች በአደራ ማስቀመጥ፤

11. በካፒታል ገበያ ውስጥ አክሲዮኖችን፣ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በገንዘብ የሚለወጡ የእዳ ሰነዶችን፣ የሚተላለፉ የንግድ ሰነዶችን፣ የክፍያ ትዕዛዞችንና የተስፋ ሰነዶችን መስጠት፣ መቀበል፣ ቀንሶ መክፈል፣ መግዛት፣ መሸጥ፤

12. ከወለድ ነጻ ባንክ አገልግሎት እና ሌሎች በየጊዜው የሚፈቀዱ ከወለድ ነጻ የባንክ ሥራዎችን ማከናወን፤

13. አግባብነት ባለው ህግ መሰረት በሌሎች የንግድ ድርጅቶች ኢንቨስት ያደርጋል፣ አስፈላጊ ሲሆንም መልሶ መሸጥ፤

14. የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎቶችን መስጠት፣ እንዲሁም ከባንኩ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ሕግ በሚፈቅደው መሰረት የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር አገልግሎት መስጠት፤

15. ከፍ ብለው ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ለአስተማማኝ የባንክ ንግድ ሥራ ጠቃሚ በሆኑና በማናቸውም ሕጋዊ ተግባራት ሁሉ ይሳተፋል።

አንቀጽ 4. ገደቦች

1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በጽሁፍ ካልፈቀደ በቀር ባንኩ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ተግባራት ማከናወን አይችልም፡-
   1.1. የንግድ ሥራውን ወይም ንብረቱን በሽያጭ ወይም በማናቸውም ዘዴ ከሌላ ተቋም ጋር ማዋሀድ ወይም በሌላ መንገድ ሕጋዊ አቋሙን የሚለውጥ ስምምነት መዋዋል፤
   1.2. ካፒታሉን መቀነስ፤
   1.3. የተቋቋመበትን መመስረቻ ጽሁፍ ማሻሻል፤
   1.4. የባንክ ንግድ ሥራ ለማካሄድ ፈቃድ የተቀበለበትን የንግድ ስም መለወጥ፤
   1.5. አግባብነት ያለው ሕግ በሚፈቅደው በተለያዩ ድርጅቶች በኢንቨስትመንት መሳተፍ፡፡
2. ከዚህ በታች ከ(ሀ) እስከ (ሐ) ለተመለከቱት ሰዎች ቀጥታ ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የሚሰጡ ብድሮች ወይም የቅድሚያ ክፍያዎች ወይም ለእነሱ የሚገቡ ማናቸውም ግዴታዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚያወጣውን መመሪያ በመከተል ይፈጸማሉ፡፡

   (ሀ) ለባንኩ የቦርድ አባላት፣ ለዋና ስራ አስፈፃሚ፣ የባንኩ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች፣ የኦዲት ዳይሬክተር፣ የሪስክ እና ኮምፕሊያስ ዳይሬክተር እንዲሁም ከላይ ከተጠቀሱት ሰዎች ጋር በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት የጋብቻና የስጋ ዝምድና ያላቸው ሰዎች በተናጠል ወይም በጥምር ወይም ከማናቸውም ሌላ ሰው ጋር ሆነው፤

   (ለ)ለባንኩ የቦርድ አባላት፣ ለዋና ስራ አስፈፃሚ፣ የባንኩ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች፣ የኦዲት ዳይሬክተር፣ የሪስክ እና ኮምፕሊያስ ዳይሬክተር እንዲሁም ከላይ ከተጠቀሱት ሰዎች ጋር በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት የጋብቻና የስጋ ዝምድና ያላቸው ሰዎች እንዲሁም ለባንኩ የቦርድ አባላት፣ ለዋና ስራ አስፈፃሚ፣ የባንኩ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ፣ የኦዲት ዳይሬክተር፣ የሪስክ እና ኮምፕሊያንስ ዳይሬክተር በባለንብረትነት፣ በዳይሬክተርነት፣ በሽርክና፣ በሥራ አስኪያጅነት በወኪልነት ወይም በአባልነት ለሚሳተፉበት የንግድ ድርጅት፣

   (ሐ)ለባንኩ የቦርድ አባላት፣ ለዋና ስራ አስፈፃሚ፣ የባንኩ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች፣ የኦዲት ዳይሬክተር፣ የሪስክ እና ኮምፕሊያስ ዳይሬክተር እንዲሁም ከላይ ከተጠቀሱት ሰዎች ጋር በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት የጋብቻና የስጋ ዝምድና ያላቸው ሰዎች ተያዥ ለሆኑዋቸው ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች፣
3. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በቅድሚያ ካልፈቀደ በስተቀር ለባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ብድር መስጠት ወይም የቦርድ አባላት ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ላሉባቸው ግዴታዎች

ዋስ መሆን ወይም ንብረቱን በዋስትና ማስያዝ አይቻልም። የባለአክሲኖች ጠቅላላ ጉባኤም ለዳይሬክተሮች ቦርድ ብድሩን ለመፍቀድ በንግድ ህጉ አንቀጽ 307 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ይሆናል።

ምዕራፍ ሁለት፡
ስለአክሲዮን፣ የባለአክሲዮኖች መብትና ግዴታ

አንቀጽ 5 የባንኩ ካፒታል

1. የባንኩ የተፈረመ አክሲዮን ካፒታል ብር 6,610,976,000.00 (ስድስት ቢሊዮን ስድስት መቶ አስር ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰባ ስድስት ሺህ) ሲሆን የእያንዳንዱ አክሲዮን ዋጋ (par-value) ብር 1000.00 (አንድ ሺህ) በሆነ 6,610,976 (ስድስት ሚሊዮን ስድስት መቶ አስር ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ስድስት) ተራ አክሲዮኖች (ordinary Shares) የተከፋፈለ ነው።
2. ከባንኩ የተፈረመ የአክሲዮን ካፒታል ውስጥ ብር 5,723,524,177.00 (አምስት ቢሊዮን ሰባት መቶ ሃያ ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሃያ አራት ሺህ አንድ መቶ ሰባ ሰባት ብር) በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል።
3. የባንኩ ካፒታልና ተቀማጭ ገንዘብ በህግ መሆን ከሚገባው በታች በሚቀንስበት ጊዜ ጉድለቱን ለማስወገድ የሚቻልበት እርምጃ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እስከሚወሰንና በካፒታሉ ላይ የታየው ቅናሽ እስከሚስተካከል ድረስ ባንኩ በማናቸውም ጊዜ የትርፍ ድርሻ አያከፋፍልም፤ ከትርፉም ላይ ምንም ዓይነት የገንዘብ ዝውውር አይፈጽምም።

አንቀጽ 6. የአክሲዮን ይዞታ

1. የባንኩ አክሲዮኖች በባለአክሲዮኑ ስም የተመዘገቡ፣ እኩል ዋጋ ያላቸውና ተራ አክሲዮኖች ይሆናሉ።
2. ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች አክሲዮን በጋራ ለመግዛት ይችላሉ። እንደዚህ በሚሆንበት ጊዜ በባንኩ ጠቅላላ ጉባዔ የሚሳተፈው ከመካከላቸው አንድ ሰው ብቻ ይሆናል።
3. የባንኩ ባለአክሲዮን መሆን የሚችሉት:-
   3.1. ማናቸውም ኢትዮጵያዊያን፣ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው ትውልደ ኢትዮጵያዊያን እና የኢትዮጵያ ሕግ የሚጠይቀውን መስፈርት የሚያሟሉ የውጭ ሀገር ዜጎች፤ እና

3.2. ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያዊያን ወይም የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያዊያን እና የኢትዮጵያ ሕግ የሚጠይቀውን መስፈርት የሚያሟሉ በውጭ ሀገር ዜጎች ባለቤትነት የተቋቋሙ ድርጅቶች ናቸው፡፡

አንቀጽ 7. የባለአክሲዮኖች መብትና ግዴታ

(1) አግባብ ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፤

(ሀ) በባለአክሲዮን ጠቅላላ ጉባዔ የመሳተፍና ድምጽ የመስጠት፤

(ለ) በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 50 መሰረት በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚፀድቀውን የትርፍ ድርሻ የማግኘት፤

(ሐ) ባንኩ በመክሰር ወይም በሌላ ምክንያት ሥራ በሚያቆምበትና ንብረቱ በሚጣራበት ጊዜ ለካፒታሉ ባዋጣው መዋጮ መጠን ተሰልቶ ከዕዳ ከተረፈው ሀብት ላይ ድርሻውን የማግኘት፤

(መ) ቃለጉባዔዎችንና የጠቅላላ ጉባዔዎችን የጉባኤው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance sheets) የመመልከትና የሀብት ዕዳ ሚዛንና የትርፍ ኪሳራ ሂሳብ ቅጂ የመውሰድ፤

(ሠ) የባንኩን ካፒታል ለመጨመር በጥሬ ገንዘብ የሚሸጡ አዳዲስ አክሲዮኖች በሚወጡበት ጊዜ በባንኩ ባሉት አክሲዮኖች ልክ ወይም ተመጣጣኝ አዲስ አክሲዮን የመግዛት የቅድሚያ መብት፡፡

(2) እያንዳንዱ ባለአክሲዮን የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፤

(ሀ) እያንዳንዱ ባለአክሲዮን በስሙ በያዛቸው አክሲዮኖች ዋጋ ልክ ለባንኩ ዕዳ ወይም ግዴታ ተጠያቂነት ያለበት ሲሆን፣ ተፈርሞ ላልተከፈለው የአክሲዮን ዋጋም አክሲዮኑን ካስተላለፈለት ሰው ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ይሆናል፡፡ ሆኖም አክሲዮኑን ለሌላ ካስተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ካለፈ ላልተከፈለው የአክሲዮን ዋጋ በኃላፊነት አይጠየቅም፡፡

(ለ) ቀሪውን የአክሲዮን ዋጋ እንዲከፍል የጊዜ ገደቡ ተገልጾ የማስጠንቀቂያ ጥሪ ከተሰጠው በኋላ ዋጋውን ካልከፈለ ባለአክሲዮን ላይ የንግድ ህግ ቁጥር 289 ከንዑስ ቁጥር 3 እስከ 7 የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

አንቀጽ 8. አክሲዮኖችን ለሌላ ስለማስተላለፍ

1. የባንኩ አክሲዮኖች ያለምንም ገደብ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፉ ይችላሉ፡፡
2. የአክሲዮኖች የባለቤትነት ዝውውር የሚከናወነው አግባብነት ባለው ህግ መሰረት በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ውስጥ የኤሌክትሮኒክስ መዝገብ ላይ እና በባንኩ የአክሲዮን መዝገብ ላይ ዝውውሩ ሲመዘገብ ነው፡፡
3. ማንኛውንም ሰው ተደማጭነት ያለው ባለአክሲዮን ሊያደርግ የሚችል የአክሲዮን ዝውውር በአክሲዮን መዝገብ ወይም በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት የኤሌክትሮኒክስ መዝገብ ውስጥ ከመመዝገቡ በፊት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት፡፡

አንቀጽ 9. የአክሲዮኖች መዝገብ

1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሰረት የባለአክሲዮኖችን ስም ዝርዝር እና ድምጽ የመስጠት መብታቸውን የሚያሳይ የውስጥ የአክሲዮን መዝገብ ባንኩ ይይዛል፡፡ መዝገቡ የባለአክሲዮኖችን ስም፣ ዜግነት፣ አድራሻ፣ የገዙትን የተፈረመና የተከፈለ አክሲዮን ብዛትና መለያ ቁጥር፣ የከፈሉትን የገንዘብ መጠንና የተመዘገቡበትን ቀን እንዲሁም አግባብነት ያላቸው የካፒታል ገበያ ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች በሚደነግጉት መሰረት አስፈላጊ የሆነ መረጃ በሙሉ መያዝ አለበት፡፡
2. በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 እና ለህዝብ የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዑዝ አልባ የማድረግ መመሪያ ቁጥር 1047/2017 እንዲሁም አዋጁን ተከትለው በሚወጡት ሌሎች መመሪያዎች መሠረት ለግዑዝ አልባ ሠነደ ሙዓለ ንዋዮች ከሚያስፈልጉት መስፈርቶች አንጻር፣ የአክሲዮን ባለቤቶች መዝገብ፣ በግልፅ (ፐብሊክ) ለገበያ የቀረቡትና እና ግዑዝ አልባ የተደረጉት ሁሉም የማህበሩን አክሲዮኖች የመጨረሻው ትክክለኛ የባለቤትነት መዝገብ በማዕከላዊ የሠነደ ሙዓለ ንዋይ ግምጃ ቤት ዘንድ ይያዛል፡፡
3. የሁሉም ባለአክሲዮኖች መረጃ ትክክለኛነትንና የተሟላ መሆንን ለማረጋገጥ ከማዕከላዊ የሠነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ጋር ተባብሮ ይሠራል፡፡ በማኅበሩ የውስጥ መዝገቦች ላይ የሚታወቅ ማንኛውም ስህተት ወይም በማዕከላዊ የሠነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት መዝገብ ላይ ሪፖርት የተደረገ ማንኛውም ስህተት ተመርምሮ ይስተካከላል፡፡ የማኅበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም አግባብነት ያለው ኃላፊ ስህተቱ ከተገኘ ወይም ከታወቀበት ጊዜ አንስቶ በሰላሳ (30) ተከታታይ ቀናት ውስጥ እንደአስፈላጊነቱ ከማዕከላዊ የሠነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ጋር በመተባበር መመርመሩንና መስተካከሉን ያረጋግጣል፡፡ የማኅበሩ

የውስጥ የአክሲዮን ባለቤቶች መዝገብ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ለተፈቀደላቸው ሰዎች ምርመራ ክፍት ይሆናሉ። የማዕከላዊ የሠነደ ሙዓለ ንዋዮች መዝገብን የመመልከት ጉዳይ በግምጃ ቤቱ የአሠራር ደንቦች እና አግባብነት ባላቸው የካፒታል ገበያ ሕጎች ይገዛል።

4. ባለአክሲዮኖችና የሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች መዝገቡን በነፃ መመልከት ይችላሉ፤ ባለአክሲዮን ያልሆነ ሌላ ሰው መዝገቡን ማየት የሚችለው ለዚህ ተብሎ ማኅበሩ የወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች ሲያሟላ ነው።

አንቀጽ 10. የአክሲዮን ግዑዝ አልባ መሆን

1. ባንኩ ያወጣቸው እና ለወደፊቱም የሚያወጣቸው አክሲዮኖች እና ማናቸውም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አግባብነት ያላቸው የካፒታል ገበያ ሕጎች በሚደነግጉት መሰረት በካፒታል ገበያ ባለስልጣን በቅድሚያ ከተመዘገቡ በኋላ ግዑዝ አልባ ይሆናሉ።
2. ለሕዝብ ለሽያጭ የሚቀርቡት ሁሉም የማኅበሩ ሠነደ ሙዓለ ንዋዮች በሕግ የሚጠየቁትን መረጃዎች በያዘው በማዕከላዊ የሠነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት በሚገኘው የኤሌክትሮኒክስ መዝገብ ውስጥ ያለውን መረጃ ያንጸባርቃሉ።
3. ባንኩ የሠነደ ሙዓለ ንዋይ የምስክር ወረቀቶችን (Physical Security Certificates) አይሰጥም። የወረቀት አክሲዮኖች ወደ ግዑዝ አልባ አክሲዮኖች የሚቀየሩበት፣ ባለቤትነት የሚረጋገጥበት እና ሌሎች ሁኔታዎች አግባብነት ባላቸው ህጎች መሠረት የሚወሰን ይሆናል።
4. የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ከዚህ በፊት ባንኩ ያወጣቸው እና ወደፊትም የሚያወጣቸውን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግዑዝ አልባ ለማድረግ የሚያስፈልገውን መስፈርት፣ግዑዝ አልባ የማድረግ ሂደቱ ምን እንደሚመስል እና ይህ ሂደት ስለሚጀመርበት ጊዜ እንዲሁም በየጊዜው ያለውን ሂደት እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ተደራሽነት ባለው ጋዜጣ እና በባንኩ ድህረ-ገጽ ለባለአክስዮኖች እንዲደርሳቸው ያደርጋል።

ምዕራፍ ሦስት፡ የባንኩ አደረጃጀት

አንቀጽ 11. የባንኩ አመራር አካላት

ባንኩ የሚከተሉት አመራር አካላት ይኖሩታል፣

1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ

2. የዳይሬክተሮች ቦርድ
3. ዋና ስራ አስፈጻሚ
4. የውጭ ኦዲተር
5. የማኅበሩ ጸሀፊ

አንቀጽ 12. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ

1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የባንኩ የበላይ አካል ሲሆን፣ በመመስረቻ ጽሁፉ፣ በንግድ ሕግና አግባብ ባላቸው ሌሎች ህጎች የተሰጡ ስልጣኖች ይኖሩታል፡፡
2. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ፣ በንግድ ሕግና በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ ከአንቀጽ 17 እስከ 28 በተወሰነው መሰረት ይካሄዳል፡፡

አንቀጽ 13. የዳይሬክተሮች ቦርድ

1. ማኅበሩ በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚሾሙ 12 (አስራ ሁለት) አባላት ባሉት የዳይሬክተሮች ቦርድ ይመራል፡፡
2. ከማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል 1/3ኛ (አራቱ) በህግ የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ ገለልተኛ ዳይሬክተሮች መሆን አለባቸው፡፡
3. ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባለት ውስጥ ቢያንስ 4 (አራት) ሴቶች መሆን አለባቸው፡፡
4. ከባንኩ ሰራተኞች በቁጥር ከ2 (ከሁለት) ያልበለጡ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆነው መመረጥ ይችላሉ፡፡
5. የማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ በተቀመጡ መስፈርቶች መሰረት ተገቢውን የትምህርት፣ የሥራ ልምድና የጾታ ስብጥርን ያሟላ መሆን ይኖርበታል፡፡ የቦርድ አባል ሆነው መመረጥ የሚችሉት አግባብነት ባላቸው ህጎች መሠረት አስፈላጊውን የብቃት እና የተገቢነት መስፈርት የሚያሟሉ ናቸው፡፡
6. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ባንኩን በአንድነት ይወክላሉ፡፡

አንቀጽ 14. ዋና ሥራ አስፈጻሚ

1. ባንኩ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾምና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚፀድቅ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ይኖረዋል፡፡
2. የባንኩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 38 እና በሌሎች ሕጎች የተመለከተው ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡ ቦርዱም እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው ሌሎች ሥልጣኖችንና ኃላፊነቶችን ሊሰጠው ይችላል፡፡

አንቀጽ 15. የውጭ ኦዲተር

የባለአአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያለው የውጭ ኦዲተር ይመርጣል፡፡ የኦዲተሩ ተግባርና ኃላፊነት በንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች እና በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 39 የተመለከተው ይሆናል፡፡

አንቀጽ 16. የማህበሩ ፀሐፊ

የማህበሩ ጸሐፊ በዚህ መመስረቻ ፅሁፍ አንቀጽ 40 እና በሌሎች ህጎች የተመለከተው ስልጣን እና ኃላፊነት ይኖረዋል፤ ተጠሪነቱም ለባንኩ ዋና ስራ ስራ አስፈፃሚ ይሆናል፡፡

ምዕራፍ አራት፡ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ

አንቀጽ 17. ጠቅላላ ደንቦች

1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ወይም አስቸኳይ ሊሆን ይችላል፡፡
2. አስፈላጊው ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ በስተቀር የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ሊካሄድና ውሳኔ ሊተላለፍ አይችልም፡፡
3. የጉባኤው ድምፅ ቆጣሪዎች የሚሆኑት፡-

3.1. ፈቃደኛ ከሆኑ በባለአክሲዮንነትም ሆነ በወኪልነት በጉባኤው ስብሰባ ላይ ከተገኙት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ባላቸው አባላት መካከል በሚደረግ ስምምነት የተወሰኑት ባለአክሲዮኖች ናቸው፡፡

3.2. በንዑስ አንቀጽ 3.1 መሰረት የድምፅ ቆጣሪ መሆን የሚችሉት ባለአክሲዮኖች ፈቃደኛ ካልሆኑ ወይም በጉባዔው የተገኙት ባለአክሲዮኖች ሌላ ሰው መምረጥ ከፈለጉ ስብሰባው እንደተጀመረ የድምፅ ቆጠራውን ለማድረግ የሚያስፈልጉ ድምፅ ቆጣሪዎችን መምረጥ አለባቸው፡፡

3.3. በንዑስ አንቀጽ 3.1 እና 3.2 የተደነገገው ቢኖርም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚደረግ ስብሰባን ድምፅ ለመቁጠር አስተማማኝ የሆነ የድምፅ ቆጠራን ለማድረግ የሚያስችል ቴክኖሎጂን መጠቀም ይቻላል፡፡

4. የንግድ ሕጉን፣ ስለባንክ ሥራ የወጣውን አዋጅ እና የባንኩን መመስረቻ ጽሁፍ መሰረት በማድረግ በጠቅላላ ጉባኤዎች የሚወሰኑ ውሳኔዎች በጉባኤው ላይ ባልተገኙት፣ በውሳኔው ባልተስማሙና ድምፅ ባልሰጡ ባለአክሲዮኖች ላይ ጭምር ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ባለአክሲዮኑ ራሱ ካልተስማማ በስተቀር አባል በመሆኑ ምክንያት ሊያገኝ የሚገባውን መሰረታዊ መብት ጠቅላላ ጉባዔው ሊነፍገው አይችልም፡፡

አንቀጽ 18. የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ

1. የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እንደነገሩ ሁኔታ በዳይሬክተሮች ቦርድ ፣ ኦዲተሮች ፣ የሂሳብ አጣሪዎች ወይም በፍ/ቤት ሊጠራ ይችላል፣
2. ከማህበሩ ገንዘብ ውስጥ ቢያንስ ከካፒታሉ አስር በመቶው (10%) በሚወከሉ ባለአክሲዮኖች ለኦዲተር ጥያቄ ሲያቀርቡ ጠቅላላ ጉባዔ ሊደረግ ይችላል፡፡
3. ከማህበሩ ገንዘብ ውስጥ ቢያንስ ከካፒታሉ አስር በመቶው (10%) ወይም ከዛ በላይ በሚወከሉ ባለአክሲዮኖች ለንግድ እና ኢንዱስተሪ ሚኒስቴር ወይም ስልጣን ላለው የመንግስት አካል ጥያቄ ሲያቀርቡ ጠቅላላ ጉባዔ ሊደረግ ይችላል፡፡
4. እንዲሁም ከማህበሩ ገንዘብ ውስጥ ቢያንስ ከካፒታሉ አምስት በመቶው (5%) በሚወከሉ ባለአክሲዮኖች ለፍርድ ቤት ጥያቄ ያቀረቡ እንደሆነና ትዕዛዝ ከተሰጠ ጠቅላላ ጉባዔ ሊጠራ ይችላል፡፡

አንቀፅ 19 የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ማስታወቂያ

1. መደበኛም ሆነ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ለመጥራት ከጉባዔው ዕለት ሃያ አራት ቀናት አስቀድሞ ሰፊ ስርጭት ባላቸው ሁለት ጋዜጦች የጉባዔ ጥሪ ማስታወቂያ እንዲሁም በባንኩ ድረ ገፅ መተላለፍ ይኖርበታል፡፡
2. ሆኖም፣ የጥሪ ማስታወቂያው ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን በአደራ ፖስታ (ሪኮማንዴ) ከተላለፈ፣ የጉባዔ ጥሪ ማታወቂያ በጋዜጣ ማውጣት አስፈላጊ አይሆንም፡፡

አንቀጽ 20. የውክልና ሰነዶች የሚቀርቡበት የጊዜ ገደብ

1. አንድ ባለአክሲዮን በተወካዩ አማካኝነት በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ሊሳተፍ ይችላል፡፡ የውክልና ሰነዶች ጠቅላላ ጉባዔ ከሚደረግበት እለት ሦስት ሙሉ ቀን አስቀድሞ ለባንኩ ዋና መ/ቤት መቅረብ አለባቸው፡፡
2. በጉባዔው ለመሳተፍ የሚያስችሉ የውክልና ፎርሞች ተሞልተው የሚላኩበት የጊዜ ገደብና ቦታው በጉባዔው ጥሪ ማስታወቂያው ላይ መገለፅ አለበት፡፡

አንቀጽ 21. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ

1. የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሂሳብ ዓመቱ በተዘጋ ከስድስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በዓመት አንድ ጊዜ መደረግ አለበት፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤዎች ሊደረጉ ይችላሉ፡፡

2. የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉትን ተግባሮች ያከናውናል፣ውሳኔ ያስተላልፋል:-
   2.1. የባንኩን የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ፤ የትርፍና ኪሣራ ሂሳብ እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድን ሪፖርት፤ የኦዲተሮችን ሪፖርት አድምጦ የማሻሻል፣ የማጽደቅ፣ ወይም ያለመቀበል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በትርፍ አመዳደብ እና አከፋፈል እንዲሁም በአጠቃላይ ያለፈውን የሂሳብ ዓመት ማጠቃለያ የተመለከቱ የሂሳብ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ያስተላልፋል፤
   2.2. በትርፍ ድርሻ አመዳደብና አከፋፈል፣ እንዲሁም ካለፈው የሂሳብ ዓመት በመነጨ የሂሳብ ነክ ጉዳዮች ላይ ሁሉ ይወስናል፡፡
   2.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ አባላትን ይሾማል፤ ይሽራል፤
   2.4. ዳይሬክተሮችን ይሾማል፣ ይሽራል፣ ክፍያቸውንም ይወስናል፡፡
   2.5. የባንኩን ኦዲተሮች ይሰይማል፣ ይሽራል፤ የሥራ ጊዜያቸውንና ክፍያቸውንም ይወስናል፡፡
   2.6. በአክሲዮን የሚለወጡ የዕዳ ሰነዶች የሚፈቀዱበትን ሁኔታና ከእነሱ ጋር የሚቀርቡትን ዋስትናዎች ያፀድቃል፡፡
   2.7. በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ወይም አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲወስንባቸው ተለይተው ከተቀመጡት ውጭ ያሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው ይወስናል፤

አንቀጽ 22. የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ምልዐተ ጉባዔ (Quorum) እና የውሳኔ አሰጣጥ

1. በመጀመሪያው የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ከጠቅላላው የባንኩ ካፒታል ቢያንስ 1/4ኛ ወይም ሃያ አምስት በመቶውን (25%) የያዙ ባለአክሲዮኖች ራሳቸውን ወይም እንደራሴዎቻቸው ካልተገኙ በቀር ምልዓተ ጉባዔ ስለማይኖር ጉባዔው ምንም ዓይነት ውሳኔ ለመወሰን አይችልም፡፡
2. ምልዓተ ጉባዔ በመጓደሉ ምክንያት መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ማካሄድ ካልተቻለ፣ ለመጀመሪያው ጉባዔ ጥሪ በተደረገበት ተመሳሳይ ሁኔታና በዚያው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሁለተኛ የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ይደረጋል፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ የተጠራው የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ምልዓተ ጉባዔ ባይኖርም በተገኙት ባለአክሲዮኖች ብቻ ጉባዔውን ለማካሄድ ይቻላል፡፡ የጉባኤው ውሳኔዎች የሚተላለፉት በጉባኤው ከተገኙት ድምፅ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች አብዛኛውን ካፒታል በሚወክሉ ድምፅ ከተደገፉ

ነው፤ ለድምፅ ብልጫ አቆጣጠር ድምፅ ያልተሰጠባቸውም ሆነ ድምፅ ያልተፃፈባቸው የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ከግምት ውስጥ አይገቡም፡፡

3. በሚካሄዱ ጉባኤዎች ሁሉ አስፈላጊው ምልዓተ ጉባኤ የሚታሰበው በህግ መሰረት ድምፅ የመስጠት መብት የሌላቸው አክሲዮኖች ከተቀነሱ በኋላ ቀሪዎቹ አክሲዮኖች በማህበሩ ዋና ገንዘብ ውስጥ ባላቸው ድርሻ ወይም መዋጮ መሰረት ነው፡፡

አንቀጽ 23. አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ

1. የማኅበሩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በማናቸውም ጊዜ ሊጠራ ይችላል፡፡
2. የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ የሚያደርጉት እንደነገሩ ሁኔታ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ ኦዲተሮች፣ ሂሳብ አጣሪዎች፣ ፍርድ ቤት ወይም ሌሎች በሕግ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ናቸው፡፡
3. በንግድ ሕግ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጐች ውስጥ የተደነገገው የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ አጠቃላይ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔው እንደአስፈላጊነቱ የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል፡-
   3.1. የመመሥረቻ ጽሁፍን ለማሻሻል፣
   3.2. የባንኩን ዋና ገንዘብ /ካፒታል/ ለመቀነስ ወይም ለመጨመር
   3.3. የባንኩን ዜግነት የመለወጥ፣
   3.4. ባንኩ እንዲፈርስ፤ ወደ ሌላ አይነት የንግድ ማህበር እንዲለወጥ፣ እንዲከፋፈል ወይም እንዲዋሀድ ለመወሰን፤

አንቀጽ 24. የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ምልዐተ ጉባዔና የውሳኔ አሰጣጥ

1. የባንኩ ዜግነት እንዲለወጥ ወይም ባለአክሲዮኖች በባንኩ ያላቸውን ኢንቨስትመንት ከፍ እንዲያደርጉ የሚጠይቁ ውሳኔዎች በሁሉም ባለአክሲዮኖች በሙሉ ድምፅ መደገፍ አለባቸው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከሚደረጉ ውሣኔዎች በስተቀር፣ በማናቸውም አስቸኳይ ጉባዔ ላይ የሚተላለፉ ሌሎች ውሣኔዎች የሚፀድቁት በጉባዔው ላይ በተገኙ ባለአክሲዮኖች ከሁለት ሦስተኛ (2/3ኛ) ባላነሰ የድምፅ ብልጫ መሠረት ሆኖ አፈፃፀሙ ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡
   2.1. በመጀመሪያው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው ባለአክሲዮኖች ውስጥ ቢያንስ የማኅበሩን ዋና ገንዘብ 1/3ኛ (አንድ ሶስተኛ) የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው ሲገኙ፣

2.2. በሁለተኛው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው ባለአክሲዮኖች ውስጥ ቢያንስ የማኅበሩን ዋና ገንዘብ 1/4ኛ (አንድ አራተኛ) የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው ሲገኙ፣

2.3. ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው ባለአክሲዮኖች የሚወክሉት ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ግምት ውስጥ ሳይገባ በተገኙት ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው ሲገኙ ይከናወናል፡፡

3. ምልዓተ ጉባዔ በመጓደሉ ምክንያት መጀመሪያ የተጠራውን አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ማካሄድ ካልተቻለ፣ ድጋሚ የጉባዔ ጥሪ ማስታወቂያ፣ አስፈላጊ ከሆነም ሦስተኛ የጉባዔ ጥሪ ማስታወቂያ በአንድ ሳምንት ልዩነት በማውጣት፣ ወይም በአማራጭ ለባለአክሲዮኖች የአደራ ደብዳቤዎች በፖስታ ቤት በመላክ የጉባዔ ጥሪ ማስተላለፍ ይቻላል፡፡

አንቀጽ 25. የጉባዔ ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ

1. በእያንዳንዱ ጉባኤ ላይ ባለአክሲዮኖች በጉባኤው ላይ መገኘታቸውን የሚያስረዳ የተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance List) መኖር አለበት፤ ሰነዱም በስብሰባው የተገኙትን ወይም ወኪል የላኩትን ባለአክሲዮኖች ስምና አድራሻቸው፤ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ያለውን የአክሲዮን መጠንና የሚሰጠውን የድምፅ ቁጥር የሚያሳይ ዝርዝር መያዝ አለበት፡፡

2. የተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ በስብሰባው መጀመሪያ ላይ በጉባኤው በአካል የተገኙ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎች የፈረሙበት ስለመሆኑ በማህበሩ ፀሐፊ መረጋገጥ አለበት፡

አንቀጽ 26. የጥቅም ግጭት

1. በራሱ ስም ወይም በሌላ ሦስተኛ ወገን በጉባዔው ላይ የሚገኝ ተሳታፊ ከባንኩ ጥቅሞች ጋር የሚጋጭ ጥቅም ያለው ሆኖ በሚኝበት ጊዜ ተሳታፊው በቀረበው ጉዳይ ላይ ድምፅ የመስጠት መብት አይኖረውም፡፡

2. ዳይሬክተሮች የራሳቸውን ኃላፊነትና ግዴታ በሚመለከት ውሳኔ ላይ ድምፅ የመስጠት መብት አይኖራቸውም፡፡

3. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አንድ ሰው ለሌላ ባለአክሲዮን እንደራሴ ሆኖ የሚሰጠውን ድምፅ እና ከባንኩ የተበደረ ባለአክሲዮን የሚኖረውን ድምፅ ለመገደብ ይችላል፡፡

4. ምልዓተ ጉባዔ በሚሰላበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፣ (2) እና (3) መሠረት ድምፅ ከመስጠት የታገዱ አክሲዮኖች ከስሌት ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡

አንቀጽ 27. ቃለጉባዔዎች

1. በጠቅላላ ጉባዔዎች ላይ የሚደረጉ ውይይቶች በቃለጉባዔ ይያዛሉ፡፡ ቃለ ጉባኤው በስብሰባው ላይ በተገኙት ዳይሬክተሮች እና በባንኩ ፀሐፊ ከተፈረመበት በኋላ በቃለ ጉባኤ መዝገብ ይገለበጣል፤ ቃለ ጉባኤው ወደ መዝገብ በትክክል ስለመገልበጡ በማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም በሌሎች ሁለት የቦርድ አባላት መረጋገጥ አለበት፡፡

2. የጠቅላላ ጉባዔ ቃለጉባዔዎች ከዚህ የሚከተሉትን ዝርዝር ነጥቦች መያዝ አለባቸው፡፡

ሀ/ ጠቅላላ ጉባዔው የተጠራበትን ምክንያት/መነሻ እንዲሁም የጉባኤው ጥሪ አደራረግ፣

ለ/ ጠቅላላ ጉባዔው የተደረገበትን ቦታና ቀን፣

ሐ/ የጠቅላላ ጉባዔውን አጀንዳ፣

መ/ በጉባኤው የተገኙ የቦርድ አባላት ስም

ሠ/ በጠቅላላ ጉባዔ የተገኙትንና የተወከሉትን አክሲዮኖች ብዛትና የምልዓተ ጉባዔውን ቁጥር፣

ረ/ ለጠቅላላ ጉባዔ የቀረቡትን ሰነዶች፣

ሸ/ የውይይቱን ፍሬ ነገር በአጭሩ፣

ቀ/ የተሰጡትን ድምፆች ውጤት፣ እና

በ/ ጉባዔው ያፀደቃቸውን ውሳኔዎች፡፡

(3) የጠቅላላ ጉባዔው ምልዓተ ጉባዔ ሳይሟላ የቀረ እንደሆነ ሰብሳቢው ይኸው ሁኔታ በቃለ ጉባዔው መዝገብ ላይ እንዲሰፍር ያደርጋል፡፡

(4) የቃለ ጉባዔዎች ቅጅዎች በዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም በስብሰባው ላይ በተገኙ ሁለት የቦርድ ዳይሬክተሮች መረጋገጥ አለባቸው፡፡

አንቀጽ 28. በጠቅላላ ጉባዔ በተሰጡ ውሣኔዎች ላይ መቃወሚያ ስለማቅረብ

1. ሕግን እና የባንኩን መመስረቻ ጽሁፍ በመተላለፍ በጠቅላላ ጉባዔ የተሰጡ ውሳኔዎች ከተወሰኑበት ቀን ጀምሮ በሦስት ወር ውስጥ መቃወሚያ ሊቀርብባቸው ይችላል፡፡ ሆኖም ውሳኔው በተግባር በዋለበት ጊዜ ሦስተኛ ወገኖች በቅን ልቦና ያገኙዋቸው መብቶች የፀኑ ሆነው ይቀጥላሉ፡፡

2. ውሳኔው እንዲሻር ወይም እንዲሰረዝ የሚቀርብ መቃወሚያ በንግድ ሕግ ቁጥር 391 ከንዑስ ቁጥር (3) እስከ (5) በተገለፀው መሠረት መሆን አለበት፡፡

ምዕራፍ አምስት

የዳይሬክተሮች ቦርድ

አንቀጽ 29. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባር

1. በሕግ የተሰጡት ስልጣን እና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ተጨማሪ ስልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   1.1. የባንኩን የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፡፡
   1.2. የማኅበሩን ስትራቴጂ እና ፖሊሲዎች ያጸድቃል፡፡
   1.3. የባንኩን ድርጅታዊ መዋቅርና የደመወዝ ስኬል ያጸድቃል፡፡
   1.4. የባንኩን ዓመታዊ በጀት እና የሥራ ዕቅድ መርመሮ ያጸድቃል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፡፡
   1.5. የባንኩን የአደጋ ተጋላጭነት እና ውስጣዊ አሰራር ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን ያረጋግጣል፡፡
   1.6. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ይጠራል፤ ዓመታዊ ሪፖርት በማዘጋጀት ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፡፡
   1.7. የባንኩን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ይሾማል፤ ይሽራል፤ የሥራ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡
   1.8. በዋና ሥራ አስፈጻሚው አቅራቢነት ለዋና ሥራ አስፈጻሚው ምክትል የሆኑ ኃላፊዎችን ይሾማል፤ ይሽራል፡፡
   1.9. የባንኩን ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ ምክትልና ከፍተኛ ስራ አስፈጻሚዎች ደመወዝ፣ አበልና ጥቅማጥቅም ይወስናል፡፡
   1.10. የባንኩን የውስጥ ኦዲት ኃላፊ፣ የሪስክና ኮምፕሊያንስ ኃላፊና አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት በቦርድ መሾም ያለባቸውን የሥራ ኃላፊዎች ይሾማል ወይም ይሽራል፡፡
   1.11. በዋና ስራ አስፈጻሚው አቅራቢነት የማኅበሩን ጸሐፊ ቅጥር እና ስንብት ያጸድቃል፡፡
   1.12. የባንኩ የውጪ ኦዲተር ሹመት እና የሥራ ዋጋ እንዲጸድቅ ለማኅበሩ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፡፡
   1.13. የባንኩ የስራ እንቅስቃሴዎች ሕግን ተከትለው መከናወናቸውን ያረጋግጣል፡፡

1.14. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ የተደነገጉ እና ለቦርዱ የተሻለ የስራ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ የቦርድ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ አባሎቻቸውን እና የስራ ኃላፊነታቸውን ይወስናል፡፡

1.15. የባንኩ ዋና ገንዘብ እንዲቀነስ ወይም እንዲጨመር ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

1.16. የቦርድ አባላትን እና የባንኩን ከፍተኛ ስራ አመራር የስራ አፈጻጸም ምዝና ስርዐት በመዘርጋት ተከታታይ ምዝናዎችን ያከናውናል፡፡

1.17. የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማ እና ምርጫ አፈጻጸም ፖሊሲ እና መመሪያ በማዘጋጀት ለጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፡፡

1.18. የባንኩን ዳይሬክተሮች ቦርድ እና የከፍተኛ ስራ ኃላፊዎች የሥነ ምግባር ደንብ እንዲሁም የባንኩን የዳይሬክተሮች ቦርድ ቻርተር ያጸድቃል፡፡

1.19. የባንኩ ሰራተኞች የሥነ-ምግባር ደንብ ጸድቆ ተግባር ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፡፡

1.20. የባንኩን የሚንቀሳቀስ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ በመስጠት ወይም ያለመያዣ ባንኩ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ሀገር አበዳሪዎች ገንዘብ እንዲበደር ለባንኩ ዋና ስራ አስፈጻሚ በቃለ-ጉባኤ ሊወክል ይችላል፡፡

1.21. አግባብነት ያለው ህግ ሲፈቅድ በውጭ አገር ቅርንጫፎች እንዲከፈቱ ወይም እንዲዘጉ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

1.22. ባንኩ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ግዥ እና ሽያጭ እንዲፈጽም ይፈቅዳል፡፡ ይህንም ሥልጣኑን ለባንኩ ዋና ስራ አስፈጻሚ በቃለ-ጉባኤ ሊወክል ይችላል፡፡

1.23. በዋና ሥራ አስፈፃሚው የሚቀርቡለት የኢንቨስትመንት እና የቋሚ ንብረትና ቴክኖሎጂ ግዥ ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

1.24. ሌሎች በሕግ፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ወይም በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

1.25. በባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በተላለፈው የካፒታል ማሳደግ ውሳኔ መሰረት በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን፣ በኢትዮጵያ ሠነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ እና በተቆጣጣሪ የመንግስት አካላት ዘንድ ማህበሩ በሠነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ የሚመዘገብበትን (Listed)፣ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ (OTC) ዘንድ የሚመዘገብበትን፣ ወይም የመጀመሪያ ዙር የህዝብ ሽያጭ (intial public offering)

የሚቀርብበት ዝርዝር ጉዳዮችን ለመወሰንና ለመቆጣጠር፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የማስመዝገብ፣ የመሸጥ፣ የመግዛት፣ በካፒታል ገበያ ባለስልጣን ህግ መሰረት "በሰነደ ሙዓለ ንዋይ መገበያየት" ተግባራት እንዲከናወኑ የማድረግ ስልጣን አለው፡፡

1.26. አግባብነት ያለው ሕግ በሚፈቅደው መሰረት ባንኩ በተለያዩ ድርጅቶች በኢንቨስትመንት እንዲሳተፍ የመወሰን ስልጣን አለው፤

1.27. ባንኩ እንዲፈርስ፣ ወደ ሌላ ዓይነት ማኅበር እንዲለወጥ ወይም ከሌላ ማኅበር ጋር እንዲዋሐድ ጥናት በማስጠናት ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

1.28. የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ማኅበሩ ያወጣቸው እና የሚያወጣቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋያት ግዑዝ-አልባ (dematerialize) ስለሚሆኑበት ሁኔታ በሚወስነው መሰረት አግባብነት ባለው ሕግ እና ሕጉን በሚያስፈፅመው አካል የሚጠየቁ ሰነዶችን እንዲዘጋጅ የማድረግ፣ የማኅበሩ ባለአክስዮኖች ሊያሟሉ የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች እንዲያሟሉ ሂደቱን እና የሚጀመርበትን ጊዜ በጋዜጣ፣ በማኅበሩ ድህረ-ገጽ እና ሌሎች አማራጮች በመጠቀም እንዲያውቁት የማስደረግ እና ባለአክሲዮኖች ስለዚሁ ሂደት ተገቢው ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎችን የማስፈፀም ሥልጣን አለው፡፡

1.29. ሌሎች በሕግ፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ወይም በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 29.1. ላይ የተዘረዘረው እንደተጠበቀ ሆኖ በሕግ ወይም በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ ለባንኩ ሌላ አካል ተለይተው ካልተሰጡ በቀር ለባንኩ የተሰጡ ስልጣን እና ተግባራትን በሙሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ያከናውናል፡፡

3. የዳይሬክተሮች ቦርድ እንደአስፈላጊነቱ ስልጣኑን ለዋና ስራ አስፈጻሚው በውክልና መስጠት ይችላል፡፡

4. የዳይሬክተሮች ቦርድ በባንኩ ውስጥ ካለ ወይም ከሌላ ከማንኛውም ሰው የሙያ ድጋፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

5. የዳይሬክተሮች ቦርድ በባንኩ ዋና ጽ/ቤት ወይም የቦርድ ሰብሳቢ በሚመርጠው ሌላ ቦታ ቢያንስ በ3 (ሶስት) ወራት ውስጥ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡ ከዚህም ሌላ የባንኩ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በሚያስፈልገው መጠን በማንኛውም ጊዜ ለመሰብሰብ ይችላል፡፡

6. የዳይሬክተሮች ቦርድ የባንኩን መመስረቻ ጽሁፍና የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባን ውሳኔ መሠረት በማድረግ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት የውስጥ ደንብ ለማዘጋጀትና በእሱ ለመመራት ይችላል፡፡

አንቀጽ 30. ለባንኩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች መዝገብ

1. የባንኩ የቦርድ አባላትን፣ ለዋና ስራ አስፈፃሚውን፣ የባንኩ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎችን፣ የኦዲት ዳይሬክተርን፣ የሪስክ እና ኮምፕሊያስ ዳይሬክተርን እንዲሁም ከላይ ከተጠቀሱት ሰዎች ጋር በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት የጋብቻና የስጋ ዝምድና ያላቸው ሰዎች እንዲሁም እነዚህ ሰዎች ባለድርሻ ወይም አመራር፣ የሆኑበት የንግድ ማህበር ወይም ድርጅት የግል ሁኔታ፣ ሙያቸውን፣ በሌሎች የንግድ ማህበራት ያላቸው ጥቅም፣ ሥራ፣ የቦርድ አባልነት ወይም ሌላ ኃላፊነት ካላቸው ይህንኑ እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን የሚያሳይ መዝገብ መያዝ አለበት፡፡
2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል፣ ኦዲተር እንዲሁም የባንኩ ፀሐፊ መዝገቡ ውስጥ በሰፈሩት ጉዳዮች ላይ ለውጥ መደረጉን ካወቀ ይህንኑ ካወቀበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ለባንኩ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
3. ባለአክሲዮኖች እና የመንግስት መ/ቤት ተወካዮች መዝገቡን በነፃ ማየት ይችላሉ፤ ባለአክሲዮን ያልሆኑ ሰዎች ለዚሁ የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈፀም መዝገቡን የማየት መብት አላቸው፡፡
4. ባንኩ የዳይሬክተሮችን ማህበራዊ አቋም፣ የተሰማሩበትን ሙያ፣ ከባንኩ ጋር ዝምድና ባላቸው በሌሎች ኩባንያዎች የሚኖራቸውን የቦርድ ዳይሬክተርነት ሁኔታ በዝርዝር የሚያሳይ የዳይሬክተሮች መዝገብ በዋና ጽ/ቤቱ መያዝ አለበት፡፡ በመዝገቡ የሰፈሩት መረጃዎች እንዲሁም የተደረጉ ማሻሻያዎች በሙሉ በመዝገቡ ላይ በሙሉ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መላክ አለባቸው፡፡

አንቀጽ 31. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ

1. የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ በዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ይመረጣሉ፡፡ የቦርዱ ሰብሳቢ መሆን የሚችለው የማኀበሩ ባለአክሲዮን የሆነ የቦርድ አባል ብቻ ነው፡፡
2. የቦርድ ሰብሳቢው በባንኩ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚሳተፍ የአስተዳደር አካል ወይም የባንኩ ሠራተኛ መሆን የለበትም፡፡

3. የባንኩ ቦርድ ሰብሳቢውን ወይም ምክትል ሰብሳቢውን በማንኛውም ጊዜ በመሻር በምትካቸው ሌላ ሰብሳቢ ወይም ምክትል ሰብሳቢ መሾም ይችላል፡፡
4. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ከቦርድ አባላት መካከል በዳይሬክተሮች ድምፅ ብልጫ ይመረጣል፡፡
5. ሰብሳቢው የቦርድን ስብሰባ ይጠራል፣ ስብሰባውንም በሊቀመንበርነት ይመራል፡፡
6. ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ም/ሰብሳቢው ወይም በቦርድ ውስጥ የአገልግሎት ብልጫ ያለው ዳይሬክተር የቦርድ ስብሰባዎችን በሰብሳቢነት ያካሂዳል፡፡ የአገልግሎት ብልጫ ያለው ከሌለ ስብሰባው ዳይሬክተሮቹ በሚሰይሙት ጊዜያዊ ሰብሳቢ ይመራል፡፡

አንቀጽ 32. የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ

1. ከአስራ ሁለቱ ዳይሬክተሮች ቢያንስ ሰባቱ በስብሰባው ካልተገኙ ወይም ካልተወከሉ በስተቀር የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ ማሳለፍ አይችልም፡፡ የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በድምፅ ብልጫ ነው፡፡ ድምጽ እኩል ለእኩል በሚከፈልበት ጊዜ የቦርድ ሰብሳቢ የደገፈው ሃሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡
2. እያንዳንዱ የቦርድ አባል በዓመት ውስጥ ቢያንስ 75% (ሰባ አምስት ከመቶ) የሚሆነውን የቦርድ ስብሰባ በአካል በመገኘት የመካፈል ግዴታ አለበት፡፡ በቦርድ ስብሰባ ለመገኘት ለማይችል ዳይሬክተር እሱ በሚሰይመው ሌላ ዳይሬክተር ብቻ ይወከላል፡፡ ውክልናው በደብዳቤ፣ በፋክስ፣ ወይም በኢሜይል ሊሰጥ ይችላል፡፡ አንድ ዳይሬክተር በአንድ ስብሰባ ላይ ከአንድ በላይ የሆኑ ዳይሬክተሮችን ወክሎ መሳተፍ አይችልም፡፡
3. የቦርዱ ውሣኔዎች በቃለ ጉባዔ ተይዘውና በስብሰባው በተገኙት ሁሉም ዳይሬክተሮች እና በማህበሩ ፀሐፊ ተፈርመው በመዝገብ ይቀመጣሉ፡፡
4. የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሣኔዎችን በሚሰጥበት ጊዜ የባለሙያ ምክር ማግኘት ካስፈለገው በባለሙያ ምክር ለመጠቀም ይችላል፡፡
5. የውሳኔዎች ቅጅዎች በቦርድ ሰብሳቢና በማህበሩ ፀሐፊ እየተረጋገጠ መፈረም አለባቸው፡፡
6. ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ያወጣል፡፡ ሁሉም ዳይሬክተሮች ለዚህ መተዳደሪያ ደንብ ተገዢ መሆን አለባቸው፡፡

አንቀጽ 33. ዳይሬክተሮችን ስለመተካት

1. በሂሣብ ዓመቱ ውስጥ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ዳይሬክተሮች ከቦርድ ከጎደሉ ቀሪዎቹ ዳይሬክተሮች በጎደሉት ዳይሬክተሮች ምትክ ሌሎች ዳይሬክተሮችን ለቀሪው

ጊዜ መሰየም ይችላሉ፡፡ የተተኪ ዳይሬክተሮች የሥራ ዘመን የሚያበቃው የጎደሉት ዳይሬክተሮች የሥራ ዘመን በሚያቃበት ጊዜ ነው፡፡

2. የጎደሉት ዳይሬክተሮች መሰየም ለሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ መጽደቅ አለበት፡፡ ጠቅላላ ጉባዔው የተተኩትን ዳይሬክተሮች ካላፀደቀ፣ በምትካቸው ሌሎች ዳይሬክተሮች መሰየም ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ስያሜው በጠቅላላው ጉባዔ ባይፀድቅም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተሰይመው ያገለገሉ ዳይሬክተሮች ባገለገሉበት ጊዜ ያከናውኗቸው ተግባሮች የፀኑ ይሆናሉ፡፡
3. ዳይሬክተሮች ጎድለው የቀሩት አባላት ከግማሽ በታች የሆኑ እንደሆነ የቀሩት አባላት የጎደሉትን አባላት ለማሾም ከጎደሉበት ጊዜ ጀምሮ በሠላሳ ቀናት ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤውን መጥራት አለባቸው፤ የጎደሉት አባላት ምትክ ሹመት እስኪደረግ ድረስ የቀሩት አባላት ማህበሩን ያስተዳድራሉ፡፡

አንቀጽ 34. የዳይሬክተሮች ቦርድ ክፍያ

1. በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ባንኩ ለዳይሬክተሮች ወርሃዊ አበልና የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡
2. ከላይ የተገለፀው ቢኖርም የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚያደርገውን ስብሰባ በአንድ ዓመት ውስጥ ቢያንስ 75%(ሰባ አምስት በመቶ) በአካል ያልተሳተፈ አባል የሥራ ዋጋ አይከፈለውም፡፡

አንቀጽ 35. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ኃላፊነት እና ተጠያቂነት

በንግድ ሕጉ እና በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ኃላፊነቶችና ተጠያቂነት ይኖርባቸዋል፡፡

1. የማሕበሩ ቦርድ አባላት ማኅበሩን እና ሁሉንም የማኅበሩ ባለአክሲዮኖች ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡
2. በሕግ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ኃላፊነታቸውን በቅን ልቦና፣ በጥንቃቄ እና በትጋት የመፈጸም ግዴታ አለባቸው፡፡
3. ማንኛውም የቦርድ አባል ከማህኅበሩ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ ከሚችሉ ሁኔታዎች ራሱን ማራቅ ይኖርበታል፡፡
4. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው ለሚደርሰው ጉዳት ለማህበሩ በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂ ናቸው፡፡

5. የዳይሬክተሮች ቦርድ በንግድ ሕጉ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እና በዚህ የመመስረቻ ጽሑፍ እንዲሁም በቦርድ ቻርተሩ መሰረት ኃላፊነትና ተጠያቂነት ይኖርበታል፡፡

አንቀጽ 36. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ስለመሻር

1. የባንኩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በማንኛውም ጊዜ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ሊሽር ወይም ሊያሰናብት ይችላል፡፡
2. በንዑስ አንቀጽ 1 እና አግባብ ባላቸው ህጎች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሻር ይችላል፡፡ እነዚህም

   2.1 በሕግ የተቀመጡ መስፈርቶችን ወይም የሥነ ስርዐት ደንቦችን በመጣስ የተመረጠ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

   2.2 ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዳይወጣ የሚያደርግ የተረጋገጠ የጤና ችግር ሲያጋጥመው፤

   2.3 በእምነት ማጉደል፣ በሙስና፣ ለመልካም ጸባይ ተቃራኒ በሆነ ወይም በሌላ ማንኛውም ተመሳሳይ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

   2.4 በበጀት ዓመቱ ከተከናወኑ የቦርድ ስብሰባዎች ቢያንስ 75 በመቶውን በአካል ያልተሳተፈ፤

   2.5 እያወቀ ከማህበሩ ጋር የጥቅም ግጭት የሚፈጥር ተግባር ሲፈጽም፤

   2.6 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ኪሳራ የደረሰበት እንደሆነ፤

   2.7 በሕግ በተቀመጡ ወይም መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው በቂ ናቸው ብሎ ባመነባቸው ሌሎች ምክንያቶች፤
3. በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አንድን የቦርድ አባል ለመሻር በቂ የሆኑ ምክንያቶች በሚከሰቱበት ወቅት የቦርድ አባሉ ከኃላፊነቱ እንዲሻር የዳይሬክተሮች ቦርድ ለባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

አንቀጽ 37. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሥራ ዘመን

1. የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሶስት (3) ዓመት ነው፡፡ የስራ ዘመናቸው የተጠናቀቀ ዳይሬክተሮች ለሁለተኛ (2) ጊዜ በድጋሚ መመረጥ ይችላሉ፡፡ ዳይሬክተሮች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ላይ በተቀመጠው መሰረት በልዩ ሁኔታ ለሶስተኛ (3ኛ) ጊዜ ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

2. በንዑስ አንቀጽ አንድ የተቀመጠው ቢኖርም አዲስ የተሾሙት ዳይሬክተሮች ሹመት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እስከሚጸድቅ ድረስ የስራ ዘመናቸው የተጠናቀቀ ዳይሬክተሮች በስራ ላይ ይቆያሉ፡፡

ምዕራፍ ስድስት

ዋና ስራ አስፈፃሚ

አንቀጽ 38. የዋና ሥራ አስፈጻሚ ሥልጣንና ተግባር

1. ባንኩ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾምና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሹመቱ የሚፀድቅ ዋና ስራ አስፈጻሚ ይኖረዋል፡፡
2. ዋና ሥራ አስፈጻሚው ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ሆኖ ደሞዝና ጥቅማጥቅሙ በዳይሬክተሮች ቦርድ ይወሰናል፡፡
3. ዋና ሥራ አስፈጻሚው ከዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ፣ በዚህ መመሥረቻ ፅሁፍና አግባብ ባላቸው ህጎች መሠረት የባንኩን አስተዳደር እና የዕለት ከዕለት ሥራ ያካሄዳል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ 1 እስከ 3 የተገለጸው ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስፈጻሚው የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡፡
    - 4.1. የባንኩን የዕለት ተዕለት ሥራ ይመራል፡፡ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ማህበሩን ይወክላል፡፡
    - 4.2. የባንኩን የዕለት ተዕለት ሥራ ለማከናወን መደበኛ የማኔጅመንት ስብሰባዎችን ያደርጋል፡፡
    - 4.3. ባንኩ ለተቋቋበት ዓላማ ግብ መምታት ተገቢውን ጥረት ያደርጋል፡፡
    - 4.4. የባንኩን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ያቅዳል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፡፡
    - 4.5. የባንኩን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድና በጀት በማዘጋጀት ለቦርድ አቅርቦ በማጸደቅ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
    - 4.6. ቦርድ የሚያፀድቀውን ስትራቴጂ እና ፖሊሲ መሰረት አድርጎ የባንኩን የአሰራር መመሪያዎችን፣ ማኑዋሎችንና የቁጥጥር ሥርዐቶችን በማጽደቅ በስራ ላይ ያውላል፡፡
    - 4.7. ትክክለኛ እና የተሟላ የሥራ ክንውን ሪፖርት በየሶስት ወሩ፣ አጠቃላይ የሂሳብ ሪፖርት በየዓመቱ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀርባል፡፡

4.8. ባንኩን ከኪሳራና ከጥፋት፣ ከድንገተኛ አደጋና ከማናቸውም ዓይነት ዕዳ ለመጠበቅ የሚያስችል የመድን ዋስትና ከታወቀ የመድን ኩባንያ ጋር ይዋዋላል፡

4.9. አስተማማኝ የኢንፎርሜሽን ሲስተም አዘጋጅቶ ለቦርድ ያቀርባል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

4.10. የባንኩን ድርጅታዊ መዋቅር በማዘጋጀት በዳይሬክተሮች ቦርድ ያጸድቃል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

4.11. በቦርድ መሾም ካለባቸው ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ውጪ በባንኩ ድርጅታዊ መዋቅር መሠረት አስፈላጊ የሆኑ የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞችን ይቀጥራል፣ ክፍያቸውን ይወስናል፣ በሕግ አግባብ ያሰናብታል፡፡

4.12. የባንኩን ምክትል ስራ አስፈጻሚዎች ሹመት ለዳይሬክተሮች ቦርድ በማቅረብ ያጸድቃል፡፡

4.13. በዳይሬክተሮች ቦርድ በተፈቀደው የአሰራር ሥርዓትና የሂሳብ አያያዝ ደንብ መሠረት ወጪዎችን ያፀድቃል፣ በሕግ የታዘዙ የመጠባበቂያ ሂሳቦችን ያቋቁማል፡፡

4.14. የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው የውክልና ስልጣን መሰረት ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ሀገር አበዳሪዎች በባንኩ ስም ብድር ይበደራል፣ የግምጃ ቤት ሰነዶችን እና ሌሎች ዕዳ ሰነዶችን ይገዛል፣ ይለውጣል ወይም ይሸጣል፡፡

4.15. ቼክ፣ የሚተላለፉ ሰነዶች፣ እንደ የሃዋላ ወረቀት ያሉ የንግድ ሠነዶችን ማውጣት፣ መፈረም፣ መቀበልና ማስተላለፍ ይችላል፡፡

4.16. የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው ውክልና መሰረት በባንኩ ስም የሚንቀሳቀሱ እና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ግዥ እና ሽያጭ ይፈፅማል፣ የግዥ እና የሽያጭ ውል ይዋዋላል፡፡ አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ ስልጣኑ ለሌላ ሶስተኛ ወገን በውክልና ይሰጣል፡፡

4.17. የባንኩን ዓላማ ለማሳደግ በሀገር ውስጥ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን ያቋቁማል፤ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ ሲሆን እንዲዘጉ ይወስናል፡፡

4.18. የሥራ መጓተትን የሚያስቀርና ትርፋማነትን የሚጨምር የተቀላጠፈ የውስጥ ቁጥጥር መዋቅርና አሠራር ይዘረጋል፡፡

4.19. በእያንዳንዱ የሂሣብ ዓመት መጨረሻ የሂሣብ ሚዛን እና የትርፍና የኪሣራ ሂሣብ መግለጫ አዘጋጅቶ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀርባል፡፡

4.20. ከተያዘው በጀት ዓመት በፊት የነበረውን የባንኩን ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ የሚመለከት ዘገባ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀርባል፡፡

4.21. የአሰሪ እና ሠራተኛ ሕግ፣ የባንኩ መመስረቻ ጽሁፍ እንዲሁም የባንኩ የሥራ ደንብ በሚፈቅዱት መሠረት በሰራተኞች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

4.22. ባንኩን ወክሎ ከሶስተኛ ወገን እና ከመንግስት አካላት ጋር ውል ይዋዋላል፤ ይፈራረማል፡፡

4.23. በባንኩ ስም የሕንጻ፣ የተሽከርካሪ ወይም ሌላ ማናቸውም ንብረት ኪራይ ውል ይፈራረማል፡፡

4.24. በባንኩ ስም በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር በሚገኙ የፋይንስ (የውጪ ምንዛሪ ጨምሮ) ሂሳብ ይከፍታል ያንቀሳቅሳል፣ በውጭ ሀገር ስለሚከፈቱት ሂሳቦች እና የገንዘብ ዓይነት ለቦርዱ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

4.25. ከቦርድ ሰብሳቢ እና ከማህበሩ ጸሐፊ ጋር በመመካከር የቦርዱን ረቂቅ የስብሰባ አጀንዳ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡

4.26. የባንኩን ጥቅም ለመጠበቅ ከባንኩ ሠራተኞች ውስጥም ሆነ ውጭ ጠበቃ ለማቆም፣ ወኪሎች ለመሾምና ሌሎች ባለሙያዎች ለመቅጠርና ለማሰናበት ይችላል፡፡

4.27. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስቀድሞ በሚወስነውና ከባንኩ ዓላማዎች ሳይወጣ በሥራ ላይ ያልዋለውን ገንዘብ ኢንቨስት ያደርጋል ወይም በአትራፊ ሥራ ላይ ያውላል፡፡

4.28. በንግድ ሕግ፣ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ወይም በዳይሬክተሮች ቦርድ የተሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

4.29. ዋና ሥራ አስፈጻሚው በመመሥረቻ ጽሁፍና በዳይሬክተሮች ቦርድ ውሣኔ መሠረት የተሰጡትን ሥልጣኖች ለባንኩ የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

ምዕራፍ ሰባት

የውጪ ኦዲተር

አንቀጽ 39. የውጭ ኦዲተር

1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያለውን የውጭ ኦዲተር መርጦ ይሰይማል፡፡
2. የባንኩ ባለአክሲዮን፣ የባንኩ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ የሆነ እንዲሁም ከእነዚህ ጋር ትዳር የመሠረተ ወይም እንደኛ ደረጃ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ወይም የሥራ ባልደረባ ወይም ሽሪክ የሆነ ሰው በውጭ ኦዲተርነት ሊመረጥ አይችልም፡፡
3. የውጭ ኦዲተሩ ለ3ት ዓመት የባንኩን ሂሳብ እንዲያጣራ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ሊሾም ይችላል ፡፡
4. ኦዲተሩ ስለ ሂሣብ ሪፖርት አቀራረብና ስለ ንብረትና ዕዳ ተመን በሚመለከተው አካል የወጡ የኦዲት መመሪያዎችን ጠብቆ ኃላፊነቱን በጥንቃቄ ማከናወን አለበት፡፡
5. የኦዲተሩ ሪፖርት ከባንኩ የበጀት ዓመት ማብቂያ በኂላ ከዘጠና ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መላክ አለበት፡፡
6. ኦዲተሩ ኃላፊነቱን በንግድ ሕጉና አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት ያከናውናል፡፡

ምዕራፍ ስምንት

የማህበሩ ፀሐፊ

አንቀጽ 40. የማህበሩ ፀሐፊ

1. ማህበሩ ተጠሪነቱ ለባንኩ ዋና ስራ አስፈፃሚ የሆነ የማህበር ፀሐፊ ይኖረዋል፡፡ የፀሐፊው ቅጥርና ስንብት በዋና ስራ አስኪያጁ አቅራቢነት በቦርዱ የሚፀድቅ ይሆናል፡፡

2. የማህበሩ ፀሐፊ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

   ሀ. የባለአክሲዮኖች እና የቦርድ አባላትን ስብሰባዎች የማዘጋጀት ፣

   ለ. ቃለ ጉባኤዎችን ማዘጋጀትና አደራጅቶ የመያዝ ፣

   ሐ. የማህበሩን መረጃዎች እና መዛግበት አደራጅቶ የመያዝ ፣

   መ. ለባለአክሲዮኖችና ለሚመለከተው አካል ሪፖርቶችንና አስፈላጊ መረጃዎች በወቅቱ የመስጠት፣

   ሠ. የባለአክሲዮኖች መዝገብ ትክክለኛነትን ማረጋገጥ፡፡

ምዕራፍ ዘጠኝ
የሂሣብ አያያዝና ተዛማጅ ተግባራት

አንቀጽ 41. ጠቅላላ መመሪያዎች

ስለ ሂሣብና መዝገብ አያያዝ በሕግ የተደነገገው ለባንክ የሂሣብና መዝገብ አያያዝም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 42. የፋይናንስ መዝገቦችና መረጃዎች

1. ባንኩ በሕግ በተደነገገው መሠረት የባንኩን የሥራ እንቅስቃሴና የገንዘብ አቋም በግልጽና በትክክል የሚያስረዱ መዝገቦች በአግባቡ መያዝና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚያወጣውን መመሪያዎችና የሚያደርገውን ሕጋዊ ቁጥጥር አክብሮ መሥራት አለበት፡፡
2. ባንኩ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ዝርዝር ጉዳዩን ወዲያውኑ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ አለበት፣
    2.1. ለገንዘብ አስቀማጮች ወይም ለሌሎች አበዳሪዎች ግዴታውን ለመፈፀም ካልቻለ፣
    2.2. ለገንዘብ አስቀማጮች ወይም ለሌሎች አበዳሪዎች የሚያደርገውን ክፍያ ለማቋረጥ ከተገደደ፡፡

አንቀጽ 43. የሂሣብ ዓመትና ሪፖርት

1. የባንኩ የሂሣብ ዓመት እ.ኤ.አ ከሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ እስከ ቀጣዩ ዓመት ሰኔ 30 ቀን ድረስ ነው፡፡
2. በእያንዳንዱ የሂሣብ ዓመት ማብቂያ ላይ ቦርዱ በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 38(4.19) መሠረት የቀረበለትን ሪፖርት መነሻ በማድረግ የባንኩን አጠቃላይ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡ ሪፖርቱም ስለባንኩ ትርፍና ኪሣራ፣ ስለ ኦዲተሮችና ዳይሬክተሮች ክፍያ፣ ስለ የመጠባበቂያ ገንዘብ ምደባና ስለ ዘመኑ የትርፍ ድርሻ አመዳደብ ዝርዝር መረጃና የውሣኔ ሃሳቦችን የያዘ መሆን አለበት፡፡

አንቀጽ 44. የሂሣብ ሰነዶችና ሪፖርት ለኦዲተሮች ስለማቅረብ

የንብረት ቆጠራ ዝርዝር፣ የሂሣብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሣራ መግለጫና የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት የባለአክሲዮኖች ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ከመደረጉ ቢያንስ ከ40 ቀናት አስቀድሞ ለኦዲተሮች እና ለንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብነት ላለው ሌላ የመንግስት መ/ቤት መተላለፍ ይኖርበታል፡፡

አንቀጽ 45. የሂሣብ ሚዛንና የትርፍና ኪሳራ መግለጫ

የሂሳብ ሚዛንና የትርፍና ኪሳራ መግለጫ፣ እንዲሁም የመተኪያና የእርጅና ዋጋ ቅነሳን የሚመለከቱ የሂሣብ መግለጫዎች አዘገጃጀት አግባብ ያላቸውን ሕጐች የተከተለ መሆን አለበት፡፡

አንቀጽ 46. የማይነካ ካፒታልና ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሣብ ስለመያዝ

1. ባንኩ በማናቸውም ጊዜ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተወሰነውን ዝቅተኛ የካፒታል መጠን መያዝ አለበት፡፡
2. የባንኩ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሣብ በየዓመቱ ከተጣራው ትርፍ ላይ ህግ የሚያዘውን ያህል በመቀነስ ይጠራቀማል፡፡ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሳቡ ከባንኩ ካፒታል ጋር እኩል በሚሆንበት ጊዜ ባንኩ በየዓመቱ ለመጠባበቂያ የሚቀንሰው መጠን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡
3. ያልተከፈለ ትርፍን፣ የተቀመጠ ገቢንና ሌሎች መጠባበቂያዎችን የሚመለከቱ ነገሮች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይፈፀማሉ፡፡
4. በሕጋዊ መጠባበቂያ የተያዘውን ሂሳብ ማጉደል ወይም ለዕዳ መክፈያ እንዲሆን ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡ ነገር ግን፣ የባንኩን ዋና ገንዘብ ለማሳደግ ሲባል ዝርዝር ሁኔታውን በማሳወቅ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስቀደሞ በሚስማማበት መሠረት ሊቀነስለት ይችላል፡፡

አንቀጽ 47. በጥሬ ገንዘብ ስለሚያዙ ሂሣቦችና የመጠባበቂያ ገንዘብ ሚዛን

1. ባንኩ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በመቶኛ (%) የተመጠነ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ (Liquid Asset) ይይዛል፡፡
2. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው በሚወስነው መጠን ባንኩ በተቀማጭ መልክ ከያዘው የሕዝብ ገንዘብ ውስጥ ለመጠባበቂያ የሚሆን ገንዘብ በብሔራዊ ባንክ ይቀመጣል፡፡

አንቀጽ 48. በቸልተኝነት ወይም እምነት በማጉደል ለሚከሰቱ ኪሣራዎች መጠባበቂያዎች

1. በማናቸውም የወንጀል ድርጊት፣ በቸልተኝነት ወይም እምነት በማጉደል በባንኩ ላይ ለሚደርስ ኪሣራ መሸፈኛ የሚሆን መጠባበቂያ ገንዘብ ባንኩ በልዩ ሂሣብ ይይዛል፡፡

2. እንዲሁም፣ ከእንደዚህ ዓይነቱ ኪሣራ ራሱን ለመጠበቅ ባንኩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚስማማበት የውል ቃል መሠረት ተገቢው ፈቃድ ካለው የታወቀ የኢንሹራንስ ድርጅት ዘንድ የመድን ዋስትና ይገባል፡፡

አንቀጽ 49. ሌሎች የመጠባበቂያ ሂሣቦች

1. ባንኩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ የሚጠይቀውን በማሟላት ቀጥሎ የተመለከቱትን ወጪዎች የሚሸፍኑ የመጠባበቂያ ሂሣቦች ይኖሩታል፡፡
    1.1. አጠራጣሪ የሆኑ ወይም ደረጃቸው የወረደ፣ ወይም የመከፈል ዕድል የሌላቸውና ከመዝገብ ያልተሰረዙ ብድሮችን የሚሸፍን፣
    1.2. ለሂሳብ ዓመቱ እና ለተጠራቀሙ ኪሳራዎች መሸፈኛ የሚሆን፣
    1.3. ባንኩን ለማደራጀት ወይም ለማስፋፋት፣ የንግድ መደብር ወይም የንግድ መልካም ስም (good will) ለመግዛት የሚደረጉ ወጪዎችን፣ አክሲዮኖችን ለመሸጥ የሚከፈለውን ኮሚሽን ጭምር የሚሸፍን፣
    1.4. በማናቸውም ሕግ መሠረት የተገቡ ግዴታዎችን በዋስትና ወይም በመያዣ ለማረጋገጥ የተሰጡ ንብረቶችን ዋጋ ለመሸፈን የሚውል፣
    1.5. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ተፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች ለተከፈለ ወጪ መሸፈኛ የሚሆን፡፡

አንቀጽ 50. የትርፍ ድርሻ አመዳደብና አከፋፈል

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስለትርፍ ክፍፍል የሚያቀርበው ሀሳብ የሂሳብ ዓመቱ በባንኩ ኦዲተሮች ከተመረመረና ከተጣራው ትርፍ ላይ ታክስ፣ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ገንዘብ፣ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ሰብሰባ የተፈቀዱ ሌሎች የመጠባበቂያ ገንዘቦች፣ ያለፉ ኪሣራዎች፣ ካለፈው ዓመት የተላለፈ ገንዘብ እና የዳይሬክተሮች ቦርድ ክፍያ ከትርፍ ድርሻ ከተቀነሰና በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ስብሰባ ከፀደቀ በኋላ የትርፍ ክፍፍሉ በአንድ ጊዜ ክፍያ ለባለአክሲዮኖች ይፈፅማል፡፡

2. ለባለአክሲዮኖች ትርፍ የሚከፋፈለው እያንዳንዱ ባለአክሲዮን የከፈለው የካፒታል መጠን እና የአክሲዮኖቹ ዋጋ በበጀት ዓመቱ ውስጥ በሙሉ ወይም በከፊል የተከፈለበትን ጊዜ መሠረት አድርጐ በማስላት ይሆናል፡፡

3. የትርፍ ድርሻ የሚከፋፈልበት ቀንና የአከፋፈሉ ሁኔታ በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ይወሰናል፡፡

4. ከፀደቀው የሂሣብ ሚዛን ውጭ ምንም ዓይነት የትርፍ ድርሻ ማከፋፈል አይፈቀድም፡፡

አንቀጽ 51. የሂሣብ ሚዛን ይፋ ስለማድረግ

1. ጊዜያዊ የሂሣብ ሚዛን ሪፖርት እና የትርፍና ኪሣራ መግለጫ የሂሣብ ዘመኑ በተዘጋ በሰላሳ ቀናት ውስጥ በፊርማ የተረጋገጠ ቅጅ ለብሔራዊ ባንክ መላክ አለበት፡፡
2. ባንኩ በኦዲተሮች የተረገገጠ የሂሳብ ሚዛንና የትርፍና ኪሣራ መግለጫ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሰራጭ ዕለታዊ ጋዜጣ እንዲታተም ያደርጋል፡፡
3. የሂሣብ ሚዛን ሪፖርት በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ከፀደቀ በኋላ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሂሣብ ሚዛኑን ቅጅና የፀደቀበትን ቃለጉባኤ የዳይሬክተሮች ቦርድ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይልካል፡፡

ምዕራፍ አስር፡ የባንኩን ካፒታል ማሳደግ ወይም መቀነስ

አንቀጽ 52. ካፒታል ስለ ማሳደግ

1. ባንኩ አስቸኳይ የባለአክሲዮኖች ስብሰባ በሚወስነው መሠረት ካፒታሉን ማሳደግ ይችላል፡፡
2. ባንኩ አዲስ አክሲዮኖች በማውጣት ካፒታሉን ሲያሳድግ፣ የአክሲዮኖች ዋጋ ከዚህ በሚከተለው ዓይነት ሊከፈል ይችላል፡፡
   2.1. በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንኩ ላይ ያሉትን ዕዳዎች በአክሲዮን በማቻቻል፣ ወይም
   2.2. የመጠባበቀያ ወይም ባንኩ የሚያዝባቸውን ሌሎች ገንዘቦች ወደ ካፒታል በማዞር፣ ወይም
   2.3. የዕዳ (የግዴታ) ሰነዶችን በአክሲዮን በመለወጥ፣
3. አዲስ የወጡ አክሲዮኖች ለሕዝብ ሲሸጡ ጥሪው በባንኩ ዳይሬክተሮች ቦርድ በተፈረመ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ (ኘሮስፔክተስ) ይፋ ይደረጋል፡፡ መግለጫው በንግድ ሕግ አንቀጽ 447 የተደነገገውን የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡
4. የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የባንኩን ካፒታል ለማሳደግ ያሳለፈው ውሣኔ በአምስት ዓመት ውስጥ ተግባራዊ ካልተደረገ ከዚያ በኃላ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

አንቀጽ 53. የቅድሚያ መብት

1. የባንኩ ባለአክሲዮኖች ቀደም ብሎ በነበራቸው የአክሲዮን መጠን ልክ በጥሬ ገንዘብ የሚሸጡ አዲስ የወጡ አክሲዮኖችን ለመግዛት የቅድሚያ መብት ይኖራቸዋል፡፡ ሆኖም ባለአክሲዮኖች በንግድ ህጉ አንቀጽ 451 መሰረት የቅድሚያ መብታቸው ስለሚገደብበት ሁኔታ ውሳኔ ማሳተላለፍ ይችላሉ፡፡

2. ባለአክሲዮኖች በቅድሚያ መብት አዲስ አክሲዮን እንዲገዙ የአክሲዮን ሽያጭ ከሚጀምርበት ቀን አስር ቀን ቀደም ብሎ በጋዜጣ እና በኤልክትሮኒክ ዘዴ እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

አንቀጽ 54. የአዲስ አክሲዮኖችን ሽያጭ የሚመለከት መረጃ ስለመያዝ

የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉትን ማረጋገጥና በሰነድ እንዲያዙ ማድረግ አለበት፡-

1. አዲስ አክሲዮኖች በሙሉ ለመገዛት መፈረማቸውን፣
2. ከአክሲዮኖቹ ዋጋ መከፈል ያለበት ገንዘብ መከፈሉን፣
3. እንዲጨመር የተወሰነው የማህበሩ ዋና ገንዘብ በሙሉ መጨመሩንና፣
4. በተጨመረው የማህበሩ ዋና ገንዘብ መሰረት የመመስረቻ ፅሑፉ መሻሻሉን፡፡

አንቀጽ 55. የካፒታል መቀነስ

በመደበኛ ተግባሩ በተከሰተ ኪሳራ ካልሆነ በቀር ካፒታሉን ለመቀነስ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የጽሁፍ ፈቃድ መገኘት አለበት፡፡

ምዕራፍ አስራ አንድ፡
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 56. ባንኩ የሚቆይበት ጊዜ

ባንኩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው፡፡

አንቀጽ 57. ከባንኩ የመውጣት መብት

የማህበሩን አላማ ወይም አይነት ለመለወጥ የተላለፈ ውሳኔን የተቃወሙ ባለአክሲዮኖች ከአባልነት ለመውጣት የፈለጉ እንደሆነ፡-

1. ውሣኔውን ባሳለፈው ጉባዔ ላይ ራሳቸው ወይም በወኪል አማካኝነት የተሳተፉ ከሆነ፣ ውሣኔ በተላለፈ በሦስት ቀናት ውስጥ፣
2. ውሣኔውን ባሳለፈው ጉባዔ ላይ ያልነበሩ ወይም ያልተወከሉ ከሆነ፣ ውሣኔውን ማስታወቂያ ለማውጣት በተፈቀደለት ጋዜጣ ይፋ በተደረገ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ በአደራ

ደብዳቤ ወይም ሌሎች አግባብነት ባላቸው ኤሌክትሮኒክ ዘዴዎች ለባንኩ ማስታወቅ አለባቸው፡፡

አንቀጽ 58. ባንኩን ለመፍረስ የሚያበቁ ምክንያቶች

1. ስለ ንግድ ማህበሮች መፍረስና ሂሣብ ማጣራት የተመለከቱት የሕግ ድንጋጌዎች በባንኩ ላይም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
2. ባንኩን የማፍረስና ሂሣብ የማጣራት ተግባር በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይንም በሚሾመው ሞግዚት ይከናወናል፡፡
3. ከሚከተሉት ምክንያቶች ውስጥ ማናቸውም ቢሆን ለባንኩ መፍረስና ሂሣብ መጣራት በቂ ሆኖ ይቆጠራል፡፡
    - 3.1. የባንኩ ዓላማ ተግባራዊ ሳይሆን ሲቀር ወይም ባንኩ ተግባሩን ለማከናወን ከአቅሙ በላይ የሆኑ ምክንያቶች ሲያጋጥሙት፣
    - 3.2. ባንኩ በፈቃደኝነት እንዲፈርስ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሲወሰን፣
    - 3.3. ባለአክሲዮኖች በሚያቀርቡት አቤቱታ መሠረት ፍርድ ቤቱ ባንኩ የሚፈርስበት በቂ ምክንያት መኖሩን በማረጋገጥ እንዲፈርስ ትዕዛዝ ሲሰጥ፣
    - 3.4. ባንኩ በመክሰሩ ምክንያት የዕዳ ማጣራትና የኪሣራ ፋይል በፍርድ ቤት ሲከፈት፣
    - 3.5. ካፒታሉ በሦስት አራተኛ (3/4ኛ) ሲቀንስ፡፡

አንቀጽ 59. በመመስረቻ ጽሁፉ ያልተሸፈኑ ጉዳዩች

በዚህ የመመስረቻ ጽሁፍ ያልተሸፈኑ ማናቸውም ጉዳዩች በንግድ ሕጉና በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጐች የተደነገጉትን በመከተል ውሣኔ ያገኛል፡፡

አንቀጽ 60. የመመስረቻ ጽሁፉን ስለማሻሻል

የሚመለከተው አካል በሚያቀርበው ሀሳብ መሠረት የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የባንኩን የመመስረቻ ጽሁፍ ለማሻሻል ይችላል፡፡ ማሻሻያው ተፈፃሚነት የሚኖረው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሲፀድቅና በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ሲመዘገብ ነው፡፡

አንቀጽ 61. የተሻሩ ድንጋጌዎች

በ2ኛ የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ፀድቆ በ05/4/2016 ዓ.ም.፣ በቁጥር ቅ8/000067/4ሀ/16 በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት የተመዘገበው የባንኩ የተሻሻለ መመስረቻ ፅሑፍ በዚህ በተሻሻለው መመስረቻ ፅሑፍ በመሻር ተተክቷል ።

አንቀፅ 62. መመስረቻ ፀሑፉ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የመመስረቻ ጽሁፍ ማሻሻያ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፀድቆ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አንቀፅ 63. የባንኩ ባለአክሲዮኖች ስም ዝርዝር፣ አደራሻ፣ ዜግነትና የአክሲዮን መጠን

የባንኩ ባለአክሲዮኖች ስም ዝርዝር፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣ የፈረሙትን የአክሲዮን ብዛትና የተከፈለውን የገንዘብ መጠን በዚህ በተሻሻለ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 9 መሠረት በተዘጋጀው የባለአክሲዮኖች መዝገብ ውስጥ የተዘረዘሩትን የሚያካትት ይሆናል።

ተ/ቁ	የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የአክሲዮን ማህበሩ ፀሐፊ ስም ዝርዝር	ኃላፊነት	ፊርማ
1	ወ/ሮ አስቴር ሰለሞን ንዋይ	ሰብሳቢ	
2	ዶ/ር በእውቀቱ ታደሰ ጎባው	ም/ሰብሳቢ	
3	ወ/ሮ ውድአላት ገዳሙ ተሻለ	አባል	
4	ወ/ሮ ብዙወርቅ ማሞ ወልደሃና	አባል	
5	ወ/ሮ እመቤት ተስፋዬ ገበያው	አባል	
6	ወ/ሮ የመንዝወርቅ ግረፌ ናርዶስ	አባል	
7	አቶ ተረፈ በዳዳ ኢታንሳ	አባል	
8	አቶ ዮሀንስ አረጋ ተፈራ	አባል	
9	አቶ አብርሃም አዱላ ኦጌ	አባል	
10	ወ/ሮ አበበች ሰረቀ ወልደአብ	አባል	
11	ወ/ሮ ማህደር ጫኔ አያሌው	አባል	
12	ወ/ሮ ፅጌ ንጋቱ አስጨናቂ	የማህበሩ ፀሐፊ	

የእናት ባንክ አ.ማ
መተዳደሪያ ደንብ

<u>የባለአክሲዮኖች መፈረሚያ ሰነድ</u>

ታህሣሥ 2004 ዓ.ም

እናት ባንክ አክሲዮን ማኅበር
የመተዳደሪያ ደንብ

እኛ ስማችን፣ ዜግነታችን፣ አድራሻችንና የአክሲዮን ይዞታችን ብዛት ከዚህ የመተዳደሪያ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ላይ የተገለፀው የእናት ባንክ አክሲዮን ማኅበር መሥራች ባለአክሲዮኖች በ1952 ዓ/ም በወጣው የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ፣ በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000፣ በመመሥረቻ ጽሑፉና በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣቸውና ወደፊትም በየጊዜው በሚያወጣቸው ደንቦችና መመሪያዎች ለመገዛትና ለመተዳደር ተስማምተን ይህን የመተዳደሪያ ደንብ ማጽደቃችንንና መፈረማችንን እናረጋግጣለን።

ምዕራፍ አንድ
ባንኩ የሚሠራቸው ሥራዎችና ገደቦች

አንቀጽ 1. ባንኩ የሚሠራቸው ሥራዎች

በመመሥረቻ ጽሑፉ አንቀጽ 3 ከተጠቀሱት ሥራዎች በተጨማሪ ባንኩ ቀጥሎ የተጠቀሱትን ሥራዎች ይሠራል።

(1) ጥያቄ ሲቀርብ የሚከፈሉ፣ የቁጠባ እና በጊዜ ገደብ የሚቀመጡ ገንዘቦችን ይቀበላል፤

(2) የተለያዩ ብድሮችንና ቅድሚያ ክፍያዎችን ይፈቅዳል፤ ሌሎች የባንክ አገልግሎቶችንም ይሰጣል፤

(3) የውጭ አገር ገንዘብ ይገዛል፤ ይሸጣል፤ ይይዛል፤ ከውጭ ምንዛሪ ጋር ግንኙት ያላቸውን ማናቸውንም ሥራዎች ይሠራል፤

(4) የግል ኩባንያዎችን የገንዘብ ዋስትና ሰነዶች ለሽያጭ ለሕዝብ ያቀርባል፤

(5) የኢትዮጵያ መንግሥት የሚያወጣቸውን የሚተላለፉ የንግድ ሰነዶች፣ የገንዘብ ዋስትና ሰነዶች፣ የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች፣ እንዲሁም ባንኩ ለሰጣቸው ብድሮችና ቅድሚያ ክፍያዎች በዋስትና የተያዙ ሌሎች ንብረቶች ሁሉ ይይዛል፤ ይገዛል፤ ይሸጣል፤

(6) ሰነዶችን፣ ዕንቁዎችን፣ የከበሩ ድንጋዮችንና ዋጋ ያላቸውን ሌሎች ነገሮች የድሬክተሮች ቦርድ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ተቀብሎ በአስተማማኝ ካዝናዎች በአደራ ያስቀምጣል፤

(7) ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በገንዘብ የሚለወጡ ሰነዶችን፣ አክሲዮኖችንና የግዴታ ሰነዶችን ይሸጣል፤ ይገዛል፤ ያስተዳድራል፤ እንዲሁም የውጪ ምንዛሪና የዋስትና ሰነዶች ግዥና ሽያጭ ሥራዎችን ያከናውናል።

(8) በራሱ ስምና ሂሳብ በንግድ ድርጅቶች ውስጥ አክሲዮኖች ይገዛል፤ አስፈላጊ ሲሆንም መልሶ ይሸጣል፤

(9) ሥራውን ለማካሄድ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ይበደራል፤

(10) የሚተላለፉ የንግድ ሰነዶችን፣ የክፍያ ትዕዛዞችንና የተስፋ ሰነዶችን ይሰጣል፤ ይቀበላል፤ ቀንሶ ይከፍላል፤ ይገዛል፤ ይሸጣል፤

(11) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በሌሎች የንግድ ድርጅቶች ኢንቨስት ማድረግ ይችላል።

(12) ከፍ ብለው በተለይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ለአስተማማኝ የባንክ ንግድ ሥራ ጠቃሚ በሆኑና በማናቸውም ሕጋዊ ተግባራት ሁሉ ይሳተፋል።

አንቀጽ 2. ገደቦች

(1) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በጽሑፍ ካልፈቀደ በቀር ባንኩ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ማድረግ አይችልም።

(ሀ) የንግድ ሥራውን ወይም ንብረቱን በሽያጭ ወይም በማናቸውም ዘዴ ከሌላ ተቋም ጋር ማዋሀድ ወይም በሌላ መንገድ ሕጋዊ አቋሙን የሚለውጥ ስምምነት መዋዋል፤

(ለ) መደበኛ ሥራውን ለማካሄድ ካልሆነ በስተቀር በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ ያለውን ንብረት በሙሉም ሆነ በከፊል ላሌላ ማስተላለፍ ወይም ከይዞታው ውጭ ማድረግ፤

(ሐ) ካፒታሉን መቀነስ፤

(መ) የተቋቋመበትን መመሥረቻ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ማሻሻል፤

(ሠ) የባንክ ንግድ ሥራ ለማካሄድ ፈቃድ የተቀበለበትን የንግድ ስም መለወጥ፤

(ረ) ባንክ ነክ ወይም ፋይናንስ ነክ ባልሆኑ ሌሎች ተግባራት ላይ መሠማራት፤

(2) ከዚህ በታች ከ(ሀ) እስከ (ሐ) ለተመለከቱት ሰዎች ቀጥታ ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የሚሰጡ ብድሮች ወይም የቅድሚያ ክፍያዎች ወይም ለእነሱ የሚገቡ ማናቸውም ግዴታዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚያወጣውን መመሪያ በመከተል ይፈጸማሉ።

(ሀ) ለድሬክተሮች፣ በተናጠል ወይም በጥምር ወይም ከማናቸውም ሌላ ሰው ጋር ሆነው፤

(ለ) ባንኩ ወይም ከድሬክተሮቹ አንዱ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑት በባለንብረትነት፣ በድሬክተርነት፣ በሽርክና፣ በሥራ አስኪያጅነት ወይም በወኪልነት ወይም በአባልነት ለሚሳተፉበት የንግድ ድርጅት፣

(ሐ) ባንኩ ወይም ከድሬክተሮቹ አንዱ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑት ተያዥ ለሆኑዋቸው ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች፣

(3) ከመደበኛ የብድር ውል በስተቀር በባንኩና በድሬክተሮች መካከል የሚደረግ ማናቸውም ውል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ካላፀደቀው በስተቀር ሕጋዊነት አይኖረውም።

ምዕራፍ ሁለት

የአክሲዮን ካፒታል፣ የባለአክሲዮኖች መብቶች እና የአክሲዮኖች መተላለፍ

አንቀጽ 3. የአክሲዮን ካፒታል

(1) የባንኩ የአክሲዮን ካፒታል በባንኩ መመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 4 የተመለከተው ይሆናል::

(2) የባንኩ ካፒታልና ተቀማጭ ገንዘብ ከሚገባው በታች በሚቀንስበት ጊዜ ጉድለቱን ለማስወገድ የሚቻልበት እርምጃ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እስከሚወሰንና በካፒታሉ ላይ የታየው ቅናሽ እስከሚስተካከል ድረስ ባንኩ በማናቸውም ጊዜ ትርፉን አያሳውቅም፣ የትርፍ ድርሻም አያከፋፍልም፣ ከትርፉም ላይ ምንም ዓይነት የገንዘብ ዝውውር አይፈጽምም::

አንቀጽ 4. የባለአክሲዮን መብቶችና ግዴታዎች

(1) አግባብ ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፤

(ሀ) በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የመሳተፍና ድምፅ የመስጠት፣

(ለ) በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 34 መሠረት በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚፀድቀውን የትርፍ ድርሻ የማግኘት፣

(ሐ) ባንኩ በመክሰር ወይም በሌላ ምክንያት ሥራ በሚያቆምበትና ንብረቱ በሚጣራበት ጊዜ ለካፒታሉ ባስገባው መዋጮ መጠን ተሰልቶ ከዕዳ ከተረፈው ሀብት ላይ ድርሻውን የማግኘት፣

(መ) ቃለጉባዔዎችንና የጠቅላላ ጉባዔዎችን የስም መዋሪያዎች (Attendance sheets) የመመልከትና የሀብትና ዕዳ ሚዛንና የትርፍና ኪሣራ ሂሳብ ቅጂ የመውሰድ፣

(ሠ) ካፒታል ለመጨመር በጥሬ ገንዘብ የሚሸጡ አዳዲስ አክሲዮኖች በሚወጡበት ጊዜ በባንኩ ባሉት አክሲዮኖች ልክ ወይም በተመጣጣኝ አዲስ አክሲዮን የመግዛት የቅድሚያ መብት::

(2) እያንዳንዱ ባለአክሲዮን የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፤

(ሀ) እያንዳንዱ ባለአክሲዮን በስሙ በያዛቸው አክሲዮኖች ዋጋ ልክ ለባንኩ ዕዳ ወይም ግዴታ ተጠያቂነት ያለበት ሲሆን፣ ተፈርሞ ሳልተከፈለው የአክሲዮን ዋጋም አክሲዮኑን ካስተላለፈለት ሰው ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ይሆናል:: ሆኖም፣ አክሲዮኑን ለሌላ ካስተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ካለፈ ላልተከፈለው የአክሲዮን ዋጋ በኃላፊነት አይጠየቅም::

(ለ) ቀሪውን የአክሲዮን ዋጋ እንዲከፍል የጊዜ ገደቡ ተገልጸ የማስጠንቀቂያ ጥሪ ከተሰጠ ው በኋላ ዋጋውን ባልከፈለ ባለአክሲዮን ላይ የንግድ ሕግ ቁጥር 342 ከንዑስ ቁጥር 3 እስከ 7 የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

(ሐ) አክሲዮኖችን በአባባ ጥቅም የያዘ ባለአባባ ያልተከፈለውን ቀሪ የአክሲዮን ገንዘብ በጥሪው መሠረት የመክፈል ግዴታ አለበት።

አንቀጽ 5. አክሲዮኖችን ለሌላ ማስተላለፍ

(1) አክሲዮን ለሌላ የሚተላለፈው የድሬክተሮች ቦርድ ባፀደቀው ቅጽ (form) መሠረት ሆኖ አክሲዮኑ ለሌላ የተላለፈ ስመሆኑ በአክሲዮን መዝገብ ላይ መጻፍ አለበት። በአክሲዮኖች መዝገብ ላይ ያልተጻፈ የአክሲዮን ማስተላለፍ ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም።

(2) አንድን ሰው ከባንኩ የተፈረመ ካፒታል ሁለት በመቶ (2%) ወይም ከዚያ በላይ ባለአክሲዮን የሚያደርግ የአክሲዮን ማስተላለፍ በአክሲዮን መዝገብ ከመመዝገቡ በፊት መተላለፉ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት።

(3) አክሲዮኖችን በጋራ ከያዙ ባለአክሲዮኖች መካከል አንዱ ቢሞት፣ በአክሲዮኖቹ ላይ መብት የሚኖራቸው በሕይወት የሚገኙት ባለአክሲዮኖችና የሟቹ ወራሾች ይሆናሉ።

ምዕራፍ ሦስት

የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ

አንቀጽ 6. ጠቅላላ ደንቦች

(1) የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ መደበኛ ወይም አስቸኳይ ሊሆን ይችላል።

(2) አስፈላጊው ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ በስተቀር የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ሊካሄድና ውሳኔ ሊተላለፍ አይችልም።

(3) አንድ ባለአክሲዮን በተወካዩ አማካይነት በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ሊሳተፍ ይችላል።

(4) ፍቃደኛ የሆኑ ሁለት ከፍተኛ አክሲዮን የያዙ ባለአክሲዮኖች ወይም ተወካዮቻቸው የጠቅላላ ጉባዔ ድምፅ ቆጣሪዎች ሆነው በጉባዔው ዕለት ይመደባሉ።

(5) የንግድ ሕጉን፣ ስለባንክ ሥራ የወጣውን አዋጅ፣ የባንኩን መመሥረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት በማድረግ በጠቅላላ ጉባዔዎች የሚወሰኑ ውሳኔዎች በጉባዔው ላይ ባልተገኙት፣ በውሳኔው ባልተስማሙትና ድምፅ ባልሰጡት ባለአክሲዮኖች ላይ ጭምር ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል። ይሁን እንጂ፣ ባለአክሲዮኑ ራሱ ካልተስማማ በስተቀር አባል በመሆኑ ምክንያት ሊያገኝ የሚገባውን መሠረታዊ መብት ጠቅላላ ጉባዔው ሊነፍገው አይችልም።

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

Authentication

አንቀጽ 7. የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ማስታወቂያ

(1) መደበኛም ሆነ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ለመጥራት ከጉባዔው ዕለት አሥራ አምስት ቀን አስቀድሞ ሰፊ ስርጭት ባላቸው ሁለት ጋዜጦች የጉባዔ ጥሪ ማስታወቂያ መተላለፍ አለበት::

(2) ሆኖም፣ የጥሪ ማስታወቂያው ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን በአደራ ፖስታ (ሪኮማንዴ) ከተላለፈ፣ የጉባዔ ጥሪ ማስታወቂያ በጋዜጣ ማውጣት አስፈላጊ አይሆንም::

አንቀጽ 8. የውክልና ሰነዶች የሚቀርቡበት የጊዜ ገደብ

(1) የውክልና ሰነዶች ጠቅላላ ጉባዔ ከሚደረግበት ዕለት ሦስት ሙሉ ቀን አስቀድሞ ለባንኩ ዋና መ/ቤት መቅረብ አለባቸው::

(2) በጉባዔው ለመሳተፍ የሚያስችሉ የውክልና ፎርሞች ተሞልተው የሚላኩበት የጊዜ ገደብና ቦታው በጉባዔ ጥሪ ማስታወቂያው ላይ መገለጥ አለበት::

አንቀጽ 9. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ

(1) የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ እንደነገሩ ሁኔታ የዳሬክተሮች ቦርድ ወይም ኦዲተሮች ወይም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያደርጉት ጥሪ መሠረት የሂሳብ ዓመቱ በተዘጋ ከስድስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በዓመት አንድ ጊዜ መደረግ አለበት::

(2) የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉትን ተግባሮች ያከናውናል፣

(ሀ) የባንኩ ዓመታዊ የሂሳብ ሚዛን፣ የትርፍና የኪሣራ መግለጫ እና የድሬክተሮችና የኦዲተሮች ሪፖርቶች በስብሰባው ላይ እንዲነበቡ ከተደረገ በኋላ ስብሰባው ያለፈውን የሂሳብ ዓመት በሚመለከት የቀረቡትን ሂሳቦች ያፀድቃል፤ ያሻሽላል ወይም ውድቅ ያደርጋል::

(ለ) በትርፍ ድርሻ አመዳደብና አከፋፈል፣ እንዲሁም ካለፈው የሂሳብ ዓመት በመነጩ የሂሳብ ነክ ጉዳዮች ላይ ሁሉ ይወስናል::

(ሐ) ድሬክተሮችን ይሾማል፣ ይሽራል፣ ክፍያቸውንም ይወስናል::

(መ) የባንኩን ኦዲተሮች ይሰይማል፣ የሥራ ጊዜያቸውንና ክፍያቸውንም ይወስናል::

(ሠ) በአክሲዮን የሚለወጡ የዕዳ ሰነዶች የሚፈቀዱበትን ሁኔታና ከእነሱ ጋር የሚቀርቡትን ዋስትናዎች ያፀድቃል::

(ረ) አስፈላጊ ሲሆን ከሥልጣኑ የተወሰነውን ለድሬክተሮች ቦርድ በውክልና ይሰጣል::

አንቀጽ 10. የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ምልዐተ ጉባዔ (Quorem) እና የውሳኔ አሰጣጥ

(1) በመጀመሪያው የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ከጠቅላላው የባንኩ ካፒታል ቢያንስ ሃያ አምስት በመቶውን (25%) የያዙ ባለአክሲዮኖች ራሳቸው ወይም እንደራሴዎቻቸው ካልተገኙ በቀር ምልዓተ ጉባዔ ስለማይኖር ጉባዔው ምንም ዓይነት ውሳኔ ለመወሰን አይችልም።

(2) ምልዓተ ጉባዔ በመጉደሉ ምክንያት መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ማካሄድ ካልተቻለ፣ ለመጀመሪያው ጉባዔ ጥሪ በተደረገበት ተመሳሳይ ሁኔታና በዚየው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሁለተኛ የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ይደረጋል። ለሁለተኛ ጊዜ የተጠራው የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ምልዓተ ጉባዔ ባይኖርም በተገኙት ባለአክሲዮኖች ብቻ ጉባዔውን ለማካሄድ ይችላል። ጉባዔውም ድምፀ ተአቅቦ ያደረጉ አክሲዮኖችን ከስሌት ውጭ በማድረግ ውሳኔዎችን በድምፅ ብልጫ የማሳለፍ ሥልጣን ይኖረዋል።

(3) ምልዓተ ጉባዔ የሚሰላው በጉባዔው ያልተወከሉትን ወይም ድምፅ የማይሰጥባቸውን አክሲዮኖች በመቀነስ ይሆናል።

አንቀጽ 11. አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ

(1) የድሬክተሮች ቦርድ ወይም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም ኦዲተሮች ወይም ቢያንስ ከካፒታሉ ሃያ በመቶውን (20%) የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ሲጠይቁ የሂሳብ ዓመቱ ከማለቁ በፊት አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሊደረግ ይችላል።

(2) እንዲሁም፣ በሂሳብ አጣሪዎች ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በተሾመ የሂሳብ አጣሪ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሊጠራ ይችላል።

(3) ከዚህ ቀጥሎ ከ(ሀ) እስከ (መ) በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ የመወሰን ሥልጣን ያለው የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሲሆን፣ ውሳኔው ተግባራዊ የሚሆነውም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሲፀድቅ ነው።

(ሀ) የመመሥረቻ ጽሑፉንና የመተዳደሪያ ደንቡን ለማሻሻል፣

(ለ) የባንኩን ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ለመቀነስ ወይም ለመጨመር፣

(ሐ) ባንኩን ከሌላ ባንክ ጋር ለማዋሀድ፣

(መ) ባንኩ እንዲፈርስና ሂሳቡ እንዲጣራ ለመወሰን፣

አንቀጽ 12. የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ምልዐተ ጉባዔና የውሳኔ አሰጣጥ

(1) የባንኩ ዜግነት እንዲለወጥ ወይም ባለአክሲዮኖች በባንኩ ያላቸውን ኢንቨስትመንት ከፍ እንዲያደርጉ የሚጠይቁ ውሳኔዎች በሁሉም ባለአክሲዮኖች በሙሉ ድምፅ መደገፍ አለባቸው።

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከሚደረጉ ውሳኔዎች በስተቀር፣ በማናቸውም አስቸኳይ ጉባዔ ላይ የሚተላለፉ ሌሎች ውሳኔዎች የሚፀድቁት በጉባዔው ላይ በተገኙ ባለአክሲዮኖች ከሁለት ሦስተኛ ($^{2}/_{3}$ኛ) ባላነሰ የድምፅ ብልጫ መሠረት ሆኖ አፈጻጸሙ ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል፣

(ሀ) በመጀመሪያው ጉባዔ ከመላው የተከፈለባቸው አክሲዮኖች ከግማሽ ያላነሱ አክሲዮኖች የያዙ ባለአክሲዮኖች ሲገኙ ወይም ሲወከሉ፣

(ለ) በሁለተኛው ጉባዔ ከመላው የተከፈለባቸው አክሲዮኖች ካአንድ ሦስተኛ ያላነሱ አክሲዮኖች የያዙ ባለአክሲዮኖች ሲገኙ ወይም ሲወከሉ፣

(ሐ) በሦስተኛው ጉባዔ ከመላው የተከፈለባቸው አክሲዮኖች ከአንድ አሥረኛ ($^{1}/_{10}$ኛ) ያላነሱ አክሲዮኖች የያዙ ባለአክሲዮኖች ሲገኙ ወይም ሲወከሉ፣

(መ) ምልዓተ ጉባዔ በመጉደሉ ምክንያት መጀመሪያ የተጠራውን አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ማካሄድ ካልተቻለ፣ ድጋሚ የጉባዔ ጥሪ ማስታወቂያ፣ አስፈላጊ ከሆነም ሦስተኛ የጉባዔ ጥሪ ማስታወቂያ በአንድ ሳምንት ልዩነት በማውጣት፣ ወይም በአማራጩ ለባለአክሲዮኖች የአደራ ደብዳቤዎች በፖስታ ሣጥን በመላክ የጉባዔ ጥሪ ማስተላለፍ ይቻላል፡፡

አንቀጽ 13. በጉባዔ የሚሳተፉ ባለአክሲዮኖች ምዝገባ

(1) በእያንዳንዱ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የተገኙት ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው የሚመዘገቡበት የስም መዋሪያ (Attendance List) መዘጋጀት አለበት፡፡ ዝርዝሩ በጉባዔው የተገኙትን ባለአክሲዮኖች ስም፣ አድራሻቸውንና እያንዳንዱ ባለአክሲዮን የያዘውን የአክሲዮን ብዛት መግለፅ አለበት፡፡

(2) የስም መዋሪያው በጉባዔው ላይ በተገኙ ባለአክሲዮኖች ወይም በወኪሎቻቸው ከተፈረመ በኋላ ስለ ትክክለኛነቱ በጉባዔው ጽ/ቤት ማረጋገጫ ይደረግበታል፡፡

አንቀጽ 14. የጥቅም ግጭት

(1) በራሱ ስም ወይም በሌላ ሦስተኛ ወገን ስም በጉባዔው ላይ የሚገኝ ተሳታፊ ከባንኩ ጥቅሞች ጋር የሚጋጭ ጥቅም ያለው ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ተሳታፊው በቀረበው ጉዳይ ላይ ድምፅ የመስጠት መብት አይኖረውም፡፡

(2) ድሬክተሮች የራሳቸውን ኃላፊነትና ግዴታ በሚመለከት ውሳኔ ላይ ድምፅ የመስጠት መብት አይኖራቸውም፡፡

(3) በአዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 13 መሠረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አንድ ሰው ለሌላ ባለአክሲዮን እንደራሴ ሆኖ የሚሰጠውን ድምፅ እና ከባንኩ የተበደረ ባለአክሲዮን የሚኖረውን ድምፅ ለመገደብ ይችላል፡፡

(4) ምልዓተ ጉባዔ በሚሰላበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሠረት ድምፅ ከመስጠት የታገዱ አክሲዮኖች ከስሌት ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡

(5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) ከተደነገጉት በስተቀር በባለአክሲዮኖች ጉባዔ ላይ የድምፅ መስጠት መብትን የሚገድብ ማናቸውም ውሳኔ ተፈጻሚነት አይኖረውም::

<u>አንቀጽ 15. ቃለጉባዔዎች</u>

(1) በጠቅላላ ጉባዔዎች ላይ የሚደረጉ ውይይቶች በቃለጉባዔ ይያዛሉ:: ቃለጉባዔዎች በጉባዔው የቢሮ አባላት በአብዛኞቹ ይፈረማሉ:: በዚህ ሁኔታ የተፈረመው ቃለጉባዔ ትክክለኛነት በድሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበርና በቦርዱ ፀሐፊ ወይም በሁለት ድሬክተሮች መረጋገጥ አለበት::

(2) የጠቅላላ ጉባዔ ቃለጉባዔዎች ከዚህ የሚከተሉትን ዝርዝር ነጥቦች መያዝ አለባቸው::

(ሀ) ጠቅላላ ጉባዔው የተጠራበትን ምክንያት ወይም መነሻ፣

(ለ) ጠቅላላ ጉባዔው የተደረገበትን ቦታና ቀን፣

(ሐ) የጠቅላላ ጉባዔውን አጀንዳ፣

(መ) የጉባዔውን የቢሮ አባላት፣

(ሠ) በጠቅላላ ጉባዔ የተገኙትንና የተወከሉትን አክሲዮኖች ብዛትና የምልዓተ ጉባዔውን ቁጥር፣

(ረ) ለጠቅላላ ጉባዔው የቀረቡትን ሰነዶች፣

(ሰ) የውይይቱን ፍሬ ነገር በአጭሩ፣

(ሸ) የተሰጡትን ድምፆች ውጤት፣ እና

(ቀ) ጉባዔው ያፀደቃቸውን ውሳኔዎች::

(3) የጠቅላላ ጉባዔው ምልዓተ ጉባዔ ሳይሟላ የቀረ እንደሆነ ሊቀመንበሩ ይኸው ሁኔታ በቃለጉባዔው መዝገብ ላይ እንዲሰፍር ያደርጋል::

(4) የቃለጉባዔዎች ቅጅዎች በድሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበርና በቦርዱ ፀሐፊ ወይም በሁለት የቦርድ ድሬክተሮች መረጋገጥ አለባቸው::

<u>አንቀጽ 16. በጠቅላላ ጉባዔ በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ መቃወሚያ ስለማቅረብ</u>

(1) ሕግን፣ የባንኩን መመሥረቻ ጽሑፍ ወይም የመተዳደሪያ ደንብ በመተላለፍ በጠቅላላ ጉባዔ የተሰጡ ውሳኔዎች ከተወሰኑበት ቀን ጀምሮ በሦስት ወር ውስጥ መቃወሚያ ሊቀርብባቸው ይችላል::

(2) ሆኖም፣ ውሳኔው በተግባር በዋለበት ጊዜ ሦስተኛ ወገኖች ባቅን ልቦና ያገኙዋቸው መብቶች የፀኑ ሆነው ይቀጥላሉ::

(3) ውሳኔው እንዲሻር ወይም እንዲሠረዝ የሚቀርብ መቃወሚያ በንግድ ሕግ ቁጥር 416 ንዑስ ቁጥር (3) እስከ (5) በተገለፀው መሠረት መሆን አለበት::

ምዕራፍ አራት

የባንኩ ሥራ አመራር

አንቀጽ 17. የድሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባር

(1) ባንኩ በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በሚመረጡ አሥራ አንድ አባላት ባሉት የድሬክተሮች ቦርድ ይመራል።

(2) ድሬክተሮቹ ለሦስት ዓመት እንዲያገለግሉ በየሦስት ዓመቱ ይመረጣሉ። ይሁን እንጂ፣ ጠቅላላ ጉባዔው በማናቸውም ጊዜ ድሬክተሮችን ለማሰናበትና አዲስ የድሬክተሮች ምርጫ ለማካሄድ ይችላል።

(3) የሥራ ጊዜውን የጨረሰ ድሬክተር እንደገና የመመረጥ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የድሬክተሮች ቦርድ ሥራ ተከታታይነት እንዲኖረው ከነባር ድሬክተሮች ውስጥ ቢበዛ አንድ ሦስተኛው እንደገና ለመመረጥ ይችላሉ።

(4) በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡት ድሬክተሮች የሥራ ዘመን መታሰብ የሚጀምረው ከተመረጡበት ቀን ጀምሮ ይሆናል። ብሔራዊ ባንክ ምርጫውን እስኪያፀድው ድረስ የነባር ድሬክተሮች የሥራ ዘመን ሳይቋረጥ ይቀጥላል።

(5) ቦርዱ ከአባላቱ መካከል ሊቀመንበር ይመርጣል።

(6) በሕግ፣ በዚህ መተዳደሪያ ደንብና በመመሥረቻ ጽሑፉ ወይም በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት ለሌላ የባንኩ አካል በተለይ የተሰጠ ካልሆነ በስተቀር፣ ለባንኩ የተሰጠ ሥልጣን የድሬክተሮች ቦርድ ሥልጣን ይሆናል።

(7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተጠቀሰው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የድሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉትን ተግባሮች ያከናውናል፤

(ሀ) የባንኩ ዓላማዎች ግባቸውን እንዲመቱ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ሁሉ ይወስዳል፣

(ለ) ባንኩ ገንዘብ እንዲበደር ይፈቅዳል፣

(ሐ) በኢትዮጵያ ውስጥና በውጭ አገር ስለሚከፈቱ ቅርንጫፎች ውሳኔ ይሰጣል፣

(መ) አስፈላጊ መስሎ የሚታየውን ማናቸውንም ሃሳብ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል።

(ሠ) የባንኩን ፕሬዝዳንት ይሾማል፣ ደመወዙን፣ አበሉንና ጥቅማጥቅሙንም ይወስናል።

(ረ) በፕሬዝዳንቱ አቅራቢነት የባንኩን ምክትል ፕሬዝዳንት ይሾማል፣ ደመወዙን፣ አበሉንና ጥቅማጥቅሙንም ይወስናል።

(ሰ) የባንኩን የሥራ አመራር ይቆጣጠራል፣

(ሸ) ለባንኩ ዓላማዎች ግብ መምታት ጠቃሚ የሆኑ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል።

(8) አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የድሬክተሮች ቦርድ ከሥልጣኑ የተወሰነውን ለይቶ ለፕሬዝዳንቱ ሊሰጥ ይችላል፡፡

(9) የድሬክተሮች ቦርድ በባንኩ ዋና ጽ/ቤት ወይም የቦርዱ ሊቀመንበር በሚመርጠው ሌላ ቦታ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡ ከዚህም ሌላ የባንኩ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በሚያስፈልገው መጠን በማንኛውም ጊዜ ለመሰብሰብ ይችላል፡፡

(10) የድሬክተሮች ቦርድ የባንኩን መመሥረቻ ጽሑፍ፣ የመተዳደሪያ ደንብና የንግድ ሕጉን መሠረት በማድረግ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት የውስጥ ደንብ ለማዘጋጀትና በእሱ ለመመራት ይችላል፡፡

(11) አንድ ድሬክተር በሕጉ፣ በመመሥረቻ ጽሑፉ፣ በመተዳደሪያ ደንቡና በጠቅላላው ስብሰባ ውሳኔ የተጣለበትን ኃላፊነት በሕጋዊ መንገድ በሚያከናውንበት ጊዜ ለፈጸመው ተግባር በኃላፊነት ወይም በዕዳ በግል ተጠያቂ አይሆንም፡፡

አንቀጽ 18. የድሬክተሮች መዝገብ

(1) ባንኩ የድሬክተሮችን ማኅበራዊ አቋም፣ የተሠማሩበትን ሙያ፣ ከባንኩ ጋር ዝምድና ባላቸው በሌሎች ኩባንያዎች የሚኖራቸውን የቦርድ ድሬክተርነት ሁኔታ በዝርዝር የሚያሳይ የድሬክተሮች መዝገብ በዋና ጽ/ቤቱ መያዝ አለበት፡፡ መዝገቡም አመቺ በሆነ ጊዜ ሁሉ ለተመልካች ክፍት መደረግ አለበት፡፡

(2) በመዝገቡ የሠፈሩት መረጃዎች እንዲሁም የተደረጉ ማሻሻያዎች በሙሉ በመዝገቡ ላይ በተጻፉ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መላክ አለባቸው፡፡

አንቀጽ 19. የድሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር

(1) የድሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር ከቦርዱ አባላት መካከል በደሬክተሮች ድምፅ ብልጫ ይመረጣል፡፡

(2) ሊቀመንበሩ የቦርዱን ስብሰባ ይጠራል፤ ስብሰባውንም በሊቀመንባርነት ይመራል፡፡

(3) ሊቀመንበሩ በማይኖርበት ጊዜ በቦርዱ ውስጥ የአገልግሎት ብልጫ ያለው ድሬክተር የቦርድ ስብሰባዎችን በሰብሳቢነት ያካሂዳል፡፡ የአገልግሎት ብልጫ ያለው ከሌለ ስብሰባው ድሬክተሮቹ በሚስይሙት ጊዜያዊ ሰብሳቢ ይመራል፡፡

አንቀጽ 20. የድሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ

(1) ከአሥራ አንዱ ድሬክተሮች ቢያንስ ስድስቱ በስብሰባው ካልተገኙ ወይም ካልተወከሉ በስተቀር የድሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ ማሳለፍ አይችልም፡፡ የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው ፍፁም በሆነ ድምጽ ብልጫ ነው፡፡

(2) በቦርድ ስብሰባ ለመገኘት የማይችል ድሬክተር እሱ በሚሰይመው ሌላ ድሬክተር ብቻ ይወከላል፡፡ ተወካዩ ድሬክተርም በራሱና በወከለው ድሬክተር ስም ድምፅ የመስጠት መብት ይኖረዋል፡፡

(3) የቦርዱ ውሳኔዎች በቃለጉባዔ ተይዘውና በስብሰባው በተገኙት ሁሉም ድሬክተሮች ተፈርመው በመዝገብ ይቀመጣሉ::

(4) የድሬክተሮች ቦርድ ውሳኔዎችን በሚሰጥበት ጊዜ የባለሙያ ምክር ማግኘት ካስፈለገው በባለሙያ ምክር ለመጠቀም ይችላል::

(5) የውሳኔዎች ቅጅዎች በቦርዱ ሊቀመንበርና በቦርዱ ፀሐፊ እየተረጋገጡ መፈረም አለባቸው::

አንቀጽ 21. ድሬክተሮችን ስለመተካት

(1) በሂሳብ ዓመቱ ውስጥ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ድሬክተሮች ከቦርዱ ከለቀቁ፣ ቀሪዎቹ ድሬክተሮች በለቀቁት ድሬክተሮች ምትክ ሌሎች ድሬክተሮችን ለቀሪው ጊዜ መሰየም ይችላሉ::

(2) ሆኖም፣ የተተኩት ድሬክተሮች ስያሜ ለሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ መጽደቅ አለበት:: ጠቅላላ ጉባዔው የድሬክተሮችን ስያሜ ካላፀደቀ፣ በምትካቸው ሌሎች ድሬክተሮች መሰየም ይችላል:: ይሁን እንጂ፣ ስያሜው በጠቅላላው ጉባዔ ባይፀድቅም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተሰይመው ያገለገሉ ድሬክተሮች በአገለገሉበት ጊዜ ያከናወኗቸው ተግባሮች የፀኑ ይሆናሉ::

(3) አብዛኞቹ ድሬክተሮች የተመረጡበትን የሥራ ዘመን ሳይጨርሱ ከቦርዱ አባልነት ከለቀቁና ቦርዱ ተግባሩን ለማከናወን የማይችልበት ሁኔታ ከተፈጠረ፣ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ተጠርቶ የጐደሉት ድሬክተሮች እንዲሟሉ ይደረጋል::

አንቀጽ 22. የድሬክተሮች ክፍያ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ባንኩ ለድሬክተሮች የትራንስፖርት አበልና የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል::

አንቀጽ 23. የባንኩ ፕሬዝዳንት ሥልጣንና ተግባር

(1) ፕሬዝዳንቱ የባንኩ ዋና ሥራ አስፈፃሚና ከፍተኛ ተጠሪ በመሆን የባንኩን አስተዳደር በበላይነት ለመምራት አጠቃላይ ሥልጣንና ኃላፊነት ተሰጥቶታል::

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ፕሬዝዳንቱ ከዚህ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

(ሀ) በባንኩ መመሥረቻ ጽሑፍ የተመለከቱትን ዓላማዎች ለማሳካት ባንኩን ወክሎ በባንኩ ስም ይሠራል፤

(ለ) ባንኩ በዓለም አቀፍና በአገር ውስጥ በሚያካሂዳቸው ሥራዎች ባንኩን በሦስተኛ ወገኖች፣ በመንግሥትና በግል ድርጅቶች፣ በባንኮችና በሌሎች የገንዘብ ተቋማት ፊት ባንኩን ይወክላል፣

(ሐ) የባንኩን ደንቦችና መመሪያዎች እያዘጋጀ ወይም እንዲዘጋጁ እያደረገ የድሬክተሮች ቦርድ እንዲያፀድቃቸው ያቀርባል፣

(መ) የባንኩን የሂሳብ አያያዝ በሚመለከት አመራር ይሰጣል፣ ተገቢውን ቁጥጥርም ያደርጋል፣

(ሠ) የባንኩን የዕለት ተዕለት ሥራ ለማከናወን መደበኛ የማኔጅመንት ስብሰባዎችን ያደርጋል፣

(ረ) በሕጉ፣ በዚህ መተዳደሪያ ደንብና በባለአክሲዮኖች ጉባዔ በተወሰነው መሠረት የተፈቀዱትን የመጠባበቂያ ሂሳቦች ያቋቁማል፣

(ሰ) የባንኩን ጥቅም ለመጠበቅ ከባንኩ ሠራተኞች ውስጥም ሆነ ውጭ ጠበቃ ለማቆም፣ ወኪሎች ለመሾምና ሌሎች ባለሙያዎች ለመቅጠርና ለማሰናበት ይችላል፣

(ሸ) ቦርዱን በቅድሚያ በማስፈቀድ በባንኩ ስም በውጭ አገርም ሆነ በአገር ውስጥ ባለ ማንኛውም ባንክ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፣

(ቀ) የሐዋላ ቼኮችን፣ የምንዛሪ ሰነዶችን፣ የተስፋ ሰነዶችን፣ ሌሎች የሚተላለፉ ሰነዶችን፣ የገቢና የወጭ ንግድ ማስታወቂያዎችን ያዘጋጃል፣ ይፈርማል፣ ይቀበላል፣ ወጭ ያደርጋል፣ ሥራ ላይ ያውላል፣ ያፀድቃል፣ ቅናሽ ያደርጋል::

(በ) ለቦርዱ በማሳወቅ ባንኩን ከኪሣራ፣ ከጥፋት፣ ከድንገተኛ አደጋና ከማናቸውም ዓይነት ዕዳ ለመጠበቅ የሚያስችል የመድን ዋስትና ከታወቀ የመድን ኩባንያ ጋር ይዋዋላል::

(ተ) የድሬክተሮች ቦርድ አስቀድሞ በሚወስነውና ከባንኩ ዓላማዎች ሳይወጣ በሥራ ላይ ያልዋለውን ገንዘብ ኢንቬስት ያደርጋል ወይም በአትራፊ ሥራ ላይ ያውላል::

(ቸ) በእያንዳንዱ የሂሳብ ዓመት መጨረሻ የሂሳብ ሚዛን እና የትርፍና የኪሣራ ሂሳብ መግለጫ ያዘጋጃል፣

(ኀ) ከተያዘው ዓመት በፊት የነበረውን የባንኩን ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ የሚመለከት ዘገባ ያቀርባል፣

(ነ) በመመሥረቻ ጽሑፉና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ መደረግ ስለሚያስፈልጋቸው ማናቸውም ማሻሻያዎች ለድሬክተሮች ቦርድ ሀሳብ ያቀርባል፣

(ኘ) ለባንኩ አመሠራረት፣ ምዝገባና ማስተዋወቂያ አስፈላጊ የሆኑትን ማናቸውንም ሕጋዊ ወጭዎችና ክፍያዎች ይፈቅዳል፣

(አ) ከቦርዱ ሊቀመንበር ጋር በመመካከር የቦርዱን ረቂቅ የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፣ የቦርድ ስብሰባዎችን ዝግጅትም ያስተባብራል::

(ከ) በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ያልተጠቀሱ ነገር ግን ለባንኩ ዓላማዎች መሳካት አስፈላጊ ያሆኑ ሌሎች ተግባሮችን ሁሉ ያከናውናል::

(3) ፕሬዝዳንቱ በመመሥረቻ ጽሑፉ፣ በዚህ መተዳደሪያ ደንብና በድሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ መሠረት የተሰጡትን ሥልጣኖች ለባንኩ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

<u>አንቀጽ 24. የባንኩ የውጭ ኦዲተር</u>

(1) የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያለውን የውጭ ኦዲተር መርጦ ይሰይማል።

(2) የባንኩ ባለአክሲዮን ወይም ድሬክተር ወይም ሠራተኛ የሆነ ወይም ከእነዚህ ጋር ትዳር የመሠረተ ወይም አንደኛ ደረጃ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ወይም የሥራ ባልደረባ ወይም ሸሪክ የሆነ ሰው በውጭ ኦዲተርነት ሊመረጥ አይችልም።

(3) የውጭ ኦዲተሩ እስከሚቀጥለው የባለአክሲዮኖች ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ድረስ በተሰየመበት ሥራ ላይ ይቆያል።

(4) ኦዲተሩ ስለ ሂሳብ ሪፖርት አቀራረብና ስለ ንብረትና ዕዳ ተመን በሚመለከተው አካል የወጡ የኦዲት መመሪያዎችን ጠብቆ ኃላፊነቱን በጥንቃቄ ማከናወን አለበት።

(5) የኦዲተሩ ሪፖርት ከባንኩ የበጀት ዓመት ማብቂያ በኋላ ከዘጠና ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መላክ አለበት።

(6) ኦዲተሩ ኃላፊነቱን በንግድ ሕጉና አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት ያከናውናል።

<u>ምዕራፍ አምስት</u>

<u>የሂሳብ አያያዝና ተዛማጅ ተግባራት</u>

<u>አንቀጽ 25. ጠቅላላ መመሪያዎች</u>

ስለ ሂሳብና መዝገብ አያያዝ በሕግ የተደነገገው ለባንኩ የሂሳብና መዝገብ አያያዝም ተፈጻሚ ይሆናል።

<u>አንቀጽ 26. የፋይናንስ መዝገቦችና መረጃዎች</u>

(1) ባንኩ በሕግ በተደነገገው መሠረት የባንኩን የሥራ እንቅስቃሴና የገንዘብ አቋም በግልጽና በትክክል የሚያስረዱ መዝገቦች በአግባቡ መያዝና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚያወጣቸውን መመሪያዎችና የሚያደርገውን ሕጋዊ ቁጥጥር አክብሮ መሥራት አለበት።

(2) ባንኩ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት ዝርዝር ጉዳዩን ወዲያውኑ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ አለበት፣

(ሀ) ለገንዘብ አስቀማጮች ወይም ለሌሎች አበዳሪዎች ግዴታውን ለመፈጸም ካልቻለ፣

(ለ) ለገንዘብ አስቀማጮች ወይም ለሌሎች አበዳሪዎች የሚያደርገውን ክፍያ ለማቋረጥ ከተገደደ፤

አንቀጽ 27. የሂሳብ ዓመትና ሪፖርት

(1) የባንኩ የሂሳብ ዓመት እ.ኤ.አ ከሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ እስከ ቀጣዩ ዓመት ሰኔ 30 ቀን ድረስ ነው:: ሆኖም፣ የባንኩ የመጀመሪያው የሂሳብ ዘመን ባንኩ ሥራ ከጀመረበት ቀን ጀምሮ እ.ኤ.አ እስከ ሰኔ 30 ቀን ድረስ ያለው ጊዜ ከስድስት ወር የሚያንስ ከሆነ የባንኩ ሂሳብ መዝጊያ ዘመን በቀጣዩ ዓመት እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን ያበቃል::

(2) በእያንዳንዱ የሂሳብ ዓመት ማብቂያ ላይ ቦርዱ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 23(2)(ቸ) መሠረት የቀረበለትን ሪፖርት መነሻ በማድረግ የባንኩን አጠቃላይ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል:: ሪፖርቱም ስለባንኩ ትርፍና ኪሣራ፣ ስለ ኦዲተሮችና ዲሬክተሮች ክፍያ፣ ስለ የመጠባበቂያ ገንዘብ ምደባና ስለ ዘመኑ የትርፍ ድርሻ አመዳደብ ዝርዝር መረጃና የውሳኔ ሀሳቦችን የያዘ መሆን አለበት::

አንቀጽ 28. የሂሳብ ሰነዶችና ሪፖርት ለኦዲተሮች ስለማቅረብ

የንብረት ቆጠራ ዝርዝር፣ የሂሳብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሣራ መግለጫና የድሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት የባለአክሲዮኖች ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ከመደረጉ ቢያንስ ከ45 ቀናት አስቀድሞ ለኦዲተሮች መቅረብ አለባቸው::

አንቀጽ 29. የሂሳብ ሚዛንና የትርፍና ኪሣራ መግለጫ

የሂሳብ ሚዛንና የትርፍና ኪሣራ መግለጫ፣ እንዲሁም የመተኪያና የእርጅና ዋጋ ቅነሳን የሚመለከቱ የሂሳብ መግለጫዎች አዘገጃጀት አግባብ ያላቸውን ሕጎች የተከተለ መሆን አለበት::

አንቀጽ 30. የማይነካ ካፒታልና ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሳብ ስለመያዝ

(1) ባንኩ በማናቸውም ጊዜ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተወሰነውን ዝቅተኛ የካፒታል መጠን መያዝ አለበት::

(2) የባንኩ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሳብ በየዓመቱ ከተጣራው ትርፍ ላይ ሃያ አምስት በመቶ (25%) በመቀነስ ይጠራቀማል:: ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሳቡ ከባንኩ ካፒታል ጋር እኩል በሚሆንበት ጊዜ ባንኩ በየዓመቱ ለመጠባበቂያ የሚቀንሰው መጠን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል::

(3) የአልተከፈለ ትርፍን፣ የተቀመጠ ገቢንና ሌሎች መጠባበቂያዎችን የሚመለከቱ ነገሮች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይፈፀማሉ::

(4) በሕጋዊ መጠባበቂያ የተያዘውን ሂሳብ ማጉደል ወይም ለዕዳ መክፈያ እንዲሆን ማስከበር የተከለከለ ነው:: ነገር ግን፣ የባንኩን ዋና ገንዘብ ለማሳደግ ሲባል ዝርዝር ሁኔታውን በማሳወቅ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስቀድሞ በሚስማማበት መሠረት ሊቀነስለት ይቻላል::

አንቀጽ 31. በጥሬ ገንዘብ ስለሚያዙ ሂሳቦችና የመጠባበቂያ ገንዘብ ሚዛን

(1) ባንኩ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በመቶኛ (%) የተመጠነ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ (liquid asset) ይይዛል::

(2) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው በሚወስነው መጠን ባንኩ በተቀማጭ መልክ ከያዘው የሕዝብ ገንዘብ ውስጥ ለመጠባበቂያ የሚሆን ገንዘብ በብሔራዊ ባንክ ይቀመጣል::

አንቀጽ 32. በቸልተኝነት ወይም እምነት በማጉደል ለሚከሰቱ ኪሣራዎች መጠባበቂያዎች

(1) በማናቸውም የወንጀል ድርጊት፣ በቸልተኝነት ወይም እምነት በማጉደል በባንኩ ላይ ለሚደርስ ኪሣራ መሸፈኛ የሚሆን መጠባበቂያ ገንዘብ ባንኩ በልዩ ሂሳብ ይይዛል::

(2) እንዲሁም፣ ከእንደዚህ ዓይነቱ ኪሣራ ራሱን ለመጠበቅ ባንኩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚስማማበት የውል ቃል መሠረት ተገቢው ፈቃድ ካለው የታወቀ የኢንሹራንስ ድርጅት ዘንድ የመድን ዋስትና ይገባል::

አንቀጽ 33. ሌሎች የመጠባበቂያ ሂሳቦች

ባንኩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ የሚጠይቀውን በማሟላት ቀጥሎ የተመለከቱትን ወጭዎች የሚሸፍኑ የመጠባበቂያ ሂሳቦች ይኖሩታል::

(1) አጠራጣሪ የሆኑ ወይም ደረጃቸው የወረደ፣ ወይም የመከፈል ዕድል የሌላቸውና ከመዝገብ ያልተሰረዙ ብድሮችን የሚሸፍን፣

(2) ለዘመኑ እና ለተጠራቀሙ ኪሣራዎች መሸፈኛ የሚሆን፣

(3) ባንኩን ለማደራጀት ወይም ለማስፋፋት፣ የንግድ መደብር ወይም የንግድ መልካም ስም (goodwill) ለመግዛት የሚደረጉትን ወጭዎችና አክሲዮኖችን ለመሸጥ የሚከፈለውን ኮሚሽን ጭምር የሚሸፍን፣

(4) በማናቸውም ሕግ መሠረት የተገቡ ግዴታዎችን በዋስትና ወይም በመያዣ ለማረጋገጥ የተሰጡ ንብረቶችን ዋጋ ለመሸፈን የሚውል፤

(5) በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ተፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች ለተከፈለ ወጭ መሸፈኛ የሚሆን::

አንቀጽ 34. የትርፍ ድርሻ አመዳደብና አከፋፈል

(1) የዲሬክተሮች ቦርድ ስለትርፍ ክፍፍል የሚያቀርበው ሀሳብ በባንኩ ኦዲተሮች ከተመረመረና በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ስብሰባ ከፀደቀ በኋላ ከተጣራው ትርፍ ላይ ታክስ፣ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ገንዘብ፣ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ስብሰባ የተፈቀዱ ሌሎች የመጠባበቂያ ገንዘቦች፣ ያለፉት ኪሣራዎች፣ ካለፈው ዓመት የተላለፈ ገንዘብ እና ለድሬክተሮች የሚከፈል የትርፍ ድርሻ ተቀንሰው የትርፍ ክፍፍሉ በአንድ ጊዜ ክፍያ ይፈጸማል::

(2) ለባለአክሲዮኖች ትርፍ የሚከፋፈለው እያንዳንዱ ባለአክሲዮን የከፈለው የካፒታል መጠን እና የአክሲዮኖቹ ዋጋ በበጀት ዓመቱ ውስጥ በሙሉ ወይም በከፊል የተከፈለበትን ጊዜ መሠረት አድርጐ በማስላት ይሆናል።

(3) የትርፍ ድርሻ የሚከፋፈልበት ቀንና የአከፋፈሉ ሁኔታ በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ይወሰናል።

(4) ከፀደቀው የሂሳብ ሚዛን ውጭ ምንም ዓይነት የትርፍ ድርሻ ማከፋፈል አይፈቀድም።

(5) አክሲዮኖች በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ሰዎች በጋራ በሚያዙበት ጊዜ ባንኩ የትርፍ ድርሻ ወይም ሌላ ክፍያ ሲፈፅም ከመካከላቸው አንዱ ገንዘቡን ከተቀበለ ለሁሉም ባለአክሲዮኖች እንደተከፈለ ይቆጠራል።

አንቀጽ 35. የሂሳብ ሚዛን ይፋ ስለማድረግ

(1) ጊዜያዊ የሂሳብ ሚዛን ሪፖርት እና የትርፍና ኪሣራ መግለጫ የሂሳብ ዘመኑ በተዘጋ በሠላሳ ቀናት ውስጥ በፊርማ የተረጋገጠ ቅጅ ለብሔራዊ ባንክ መላክ አለበት።

(2) ባንኩ በኦዲተሮች የተረጋገጠ የሂሳብ ሚዛንና የትርፍና ኪሣራ መግለጫ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሰራጭ ዕለታዊ ጋዜጣ እንዲታተም ያደርጋል።

(3) የሂሳብ ሚዛን ሪፖርት በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በጸደቀ በሠላሳ ቀናት ውስጥ የሂሳብ ሚዛኑን ቅጅና የጸደቀበትን ቃለጉባዔ የድሬክተሮች ቦርድ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ይልካል።

ምዕራፍ ስድስት

የባንኩን ካፒታል ማሳደግ ወይም መቀነስ

አንቀጽ 36. ካፒታል ስለ ማሳደግ

(1) ባንኩ በአስቸኳይ የባለአክሲዮኖች ስብሰባ በሚወስነው መሠረት ካፒታሉን ማሳደግ ይችላል።

(2) ባንኩ አዲስ አክሲዮኖች በማውጣት ካፒታሉን ሲያሳድግ፣ የአክሲዮኖቹ ዋጋ ከዚህ በሚከተለው ዓይነት ሊከፈል ይችላል።

(ሀ) በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንኩ ላይ ያሉትን ዕዳዎች በአክሲዮን በማቻቻል፣ ወይም

(ለ) የመጠባበቂያ ወይም ባንኩ የሚያዝባቸውን ሌሎች ገንዘቦች ወደ ካፒታል በማዞር፣ ወይም

(ሐ) የዕዳ (የግዴታ) ሰነዶችን በአክሲዮን በመለወጥ፣

(3) አዲስ የወጡ አክሲዮኖች ለሕዝብ የሚሸጡ ከሆነ፣ ለሕዝብ የሚደረገው ጥሪ በባንኩ ተወካይ በተፈረመ መግለጫ (ፕሮስፔክተስ) ይፋ ይደረጋል። የተባለው መግለጫ በንግድ ሕግ ቁጥር 469 የተደነገገውን የሚያሟላ መሆን አለበት።

(4) አዲስ አክሲዮኖችን ለመግዛት ለባንኩ የሚቀርብ ማንኛውም የጽሑፍ ማመልከቻ ቢያንስ የሚገዙትን አክሲዮኖች ጠቅላላ ዋጋ አንድ አራተኛ (¼ኛ) ወዲያውኑ ለመክፈል ከሚያስችል ገንዘብ ጋር ካልቀረበ በስተቀር ተቀባይነት አይኖረውም::

(5) የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የባንኩን ካፒታል ለማሳደግ ያሳለፈው ውሳኔ በአምስት ዓመት ውስጥ ተግባራዊ ካልተደረገ ከዚያ በኋላ ተፈጻሚነት አይኖረውም::

አንቀጽ 37. <u>የቅድሚያ መብት</u>

የባንኩ ባለአክሲዮኖች ቀደም ብሎ በነበራቸው የአክሲዮን መጠን ልክ በጥሬ ገንዘብ የሚሸጡ አዲስ የወጡ አክሲዮኖችን ለመግዛት የቅድሚያ መብት ይኖራቸዋል:: የአክሲዮኖች ሽያጭ የሚጀመርበት ቀን ይፋ ከመሆኑ ከሠላሳ ቀናት በፊትም ይኸው በአደራ ደብዳቤ ለባለአክሲዮኖች እንዲደርሳቸው ይደረጋል::

አንቀጽ 38. <u>የአዲስ አክሲዮኖችን ሽያጭ የሚመለከት መረጃ ስለመያዝ</u>

የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉትን የሚያካትት መረጃ (ሪከርድ) ይይዛል::

(1) አዲስ አክሲዮኖች በሙሉ መሸጣቸውንና ዋጋቸው ተጠናቆ መከፈሉን የሚያረጋግጥ፣

(2) የተፈቀደው የካፒታል ጭማሪ በተግባር መከናወኑን የሚያሳይ፣ እና

(3) የካፒታሉን ጭማሪ በሚመለከት ተገቢው ማሻሻያ በመመሥረቻ ጽሑፉና በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ መጻፉን የሚያረጋግጥ::

አንቀጽ 39. <u>የካፒታል መቀነስ</u>

በመደበኛ ተግባሩ በተከሰተ ኪሣራ ካልሆነ በቀር ካፒታሉን ለመቀነስ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የጽሁፍ ፈቃድ መገኘት አለበት::

<u>ምዕራፍ ሰባት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

አንቀጽ 40. <u>ከባንኩ የመውጣት መብት</u>

ባለአክሲዮኖች ከአባልነት ለመውጣት በሚፈልጉበት ጊዜ ከአክሲዮን ማኅበሩ ለመውጣት መፈለጋቸውን ከዚህ በታች በ(ሀ) እና በ(ለ) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በአደራ ደብዳቤ ለባንኩ ማስታወቅ አለባቸው::

(ሀ) ውሳኔውን ባሳለፈው ጉባዔ ላይ ራሳቸው ወይም በወኪል አማካይነት የተሳተፉ ከሆነ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ውሳኔ በተላለፈ ገሦስት ቀናት ውስጥ፣

(ለ) ውሳኔውን ባሳለፈው ጉባዔ ላይ ያልነበሩ ወይም ያልተወከሉ ከሆነ፣ ውሳኔው ማስታወቂያ ለማውጣት በተፈቀደለት ጋዜጣ ይፋ በተደረገ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ::

አንቀጽ 41. የባንኩ መፍረስና ባንኩን ለመፍረስ የሚያበቁ ምክንያቶች

(1) ስለ ንግድ ማኅበሮች መፍረስና ሂሳብ ማጣራት የተመለከቱት የሕግ ድንጋጌዎች በባንኩ ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ::

(2) ባንኩን የማፍረስና ሂሳብ የማጣራት ተግባር በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይንም በሚሾመው ሞግዚት ይከናወናል::

(3) ከሚከተሉት ምክንያቶች ውስጥ ማናቸውም ቢሆን ለባንኩ መፍረስና ሂሳብ መጣራት በቂ ሆኖ ይቆጠራል::

(ሀ) የባንኩ ዓላማ ተግባራዊ ሳይሆን ሲቀር ወይም ባንኩ ተግባሩን ለማከናወን ከአቅሙ በላይ የሆኑ ምክንያቶች ሲያጋጥሙት፣

(ለ) ባንኩ በፈቃደኝነት እንዲፈርስ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሲወሰን፣

(ሐ) አንድ ባለአክሲዮን በሚያቀርበው አቤቱታ መሠረት ፍርድ ቤቱ ባንኩ የሚፈርስበት በቂ ምክንያት መኖሩን በማረጋገጥ እንዲፈርስ ትዕዛዝ ሲሰጥ፣

(መ) ባንኩ በመክሰሩ ምክንያት የዕዳ ማጣራትና የኪሣራ ፋይል በፍርድ ቤት ሲከፈት፣

(ሠ) ካፒታሉ በሦስት አራተኛ ($^3/_4$ኛ) ሲቀንስ::

አንቀጽ 42. በመተዳደሪያ ደንቡ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች

በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ ያልተሸፈኑ ማናቸውም ጉዳዮች በመመሥረቻ ጽሑፉ፣ በንግድ ሕጉና በሌሎች አግባብ ባለቸው ሕጎች የተደነገጉትን በመከተል ውሳኔ ያገኛሉ::

አንቀጽ 43. የመተዳደሪያ ደንቡን ስለማሻሻል

የሚመለከተው አካል በሚያቀርበው ሀሳብ መሠረት የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የባንኩን የመተዳደሪያ ደንብ ለማሻሻል ይችላል:: ማሻሻያው ተፈጻሚነት የሚኖረው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሲፈቅድና በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ሲመዘገብ ነው::

አንቀጽ 44. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የመተዳደሪያ ደንብ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፀድቆ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

በኢፌዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር
የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት
አዲስ አበባ (ዋናው መሥሪያ ቤት)

ቁጥር ቀ/ጠ/2222/40/2005

በጽሕፈት ቤቱ ቀርበው ፈርመዋል ።

አዲስ አበባ 08/02 ቀን 2005 ዓ.ም.

ይርጋ ታደሰ
የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ
ጽ/ቤት ኃላፊ

በኢፌዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት
The FDRE Ministry of Justice Documents Authentication and Registration Office

በ[illegible] የፍትህ ሚኒስቴር
የሰነዶች [illegible]ና ምዝገባ ጽ/ቤት
[illegible] አበባ

የቴምብር ቀረጥ ማረጋገጫ ማህተም

የተከፈለ[illegible] መክፈያ [illegible] 13258=
[illegible]
የሰነ[illegible] ቴምብር ተለጥፏል ።
[illegible] 417891
09/2 ቀን 2001 ዓ.ም.
የቴምብር ቀረጥ ሠብሳቢ [illegible]

ስም [signature]

ፊርማ